# መሪዎችን ማሳደግ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገረ መለኮት

**ሕጉ**


©2023 HTTP



## 1. የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያው ክፍል ሕግ በመባል ይታወቃል

ኢየሱስ አሁን ብሉይ ኪዳን በምንለው ውስጥ ሦስት የተለያዩ ክፍሎችን ጠቅሷል (**ሉቃስ 24፡25–27፣ 44–48** ይመልከቱ)። ምንም እንኳን በውስጡ ሁሉንም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ያሉት አንድ መጽሐፍ እንኳ ባይኖረውም፣ ነገር ግን ኢየሱስ ቅዱሳት መጻሕፍትን አንድ መጽሐፍ እንደሆኑ አድርጎ ይጠቅስ ነበር፤ ስለዚህም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሦስት ክፍሎችን ያውቅ እንደነበር ግልጽ ነው። ኢየሱስ ሁሉንም የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት የያዘ አንድም መጽሐፍ ያልበረው፤ እርሱ በነበረበት ጊዜ ቅዱሳት መጽሕፍት በብራና ጥቅልል ላይ ብቻ ይጻፉ ስለነበረም ነው። ደግሞ በወቅቱ  የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች የተካተቱበት ሁሉንም አጠቃሎ መያዝ የሚችል ረጅም የብራና ጥቅልልም ባለመኖሩ ምክንያት ጭምር ነበር። ሉቃስ በሐዋሪያት ሥራ በጻፈው መሠረት ጳውሎስም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተለያዩ ክፍሎች እንዳሉ ተገንዝቦ እንደነበር ግልጽ ነው (**የሐዋሪያት ሥራ 24፡14 እና 28፡23** ይመልከቱ)።

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ክፍል ሕግ ይባላል። በሕጉ ውስጥ የተካተቱ አምስት መጽሐፍት አሉ፤ እነርሱም ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘጸአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቁ እና ኦሪት ዘዳግም ናቸው። እነዚህም አንዳንድ ጊዜ የሙሴ መጽሐፍት ወይም ፔንታቱክ በመባል ይታወቃሉ። የብሉይ ኪዳንም ሆነ የአዲስ ኪዳን ጻሐፍት ሙሴ የሕጉ ጸሐፊ እንደሆነ ያስረግጣሉ። ሕጉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት አምስቱ ክፍሎች የተለየ ነው፤ ምክንያቱም አምስቱንም ክፍሎች የተወሰዱት ከሕጉ ነውና። ሕጉ በመጀመሪያ የተጻፈ ስልሆነ ከዚያ በኋላ ከተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት ምንም አይጠቅስም። ይልቁንም ሕጉ በተቀሩት ቅዱሳን መጽሐፎች ውስጥ ተደጋግሞ ተጽፎአል (ወይም ተጠቅሷል)።



## 2. በሕጉ ውስጥ ያሉትን የእያንዳንዱ መጽሐፍ ማጠቃለያ


***ኦሪት ዘፍጥረት*** – ይህ መጽሐፍ ስለ ፍጥረት፣ የሰው ልጆች ውደቀት፣ ከገነት ውጭ ያለውን ሕይወት፣ ስለ ዓለም አቀፋዊው ጎርፍ እና እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ልዩ ቃል ኪዳን መመስረትን ይናግራል። እንደዚሁም መጽሐፉ ስለ አብርሐም ታላላቅ የልጅ ልጆች በማስመልከት ገለፃ በማድረግ ይጠናቀቃል።

***ኦሪት ዘፀአት*** – ይህ የእሥራኤልውያን የግብፅ ሕይወትና ከግብፅ ነፃ መውጣታቸውን እና የማደሪያውን ድንኳን መገንባትንና የክህነት አመሰራረት ይገልጻል።

***ኦሪት ዘሌዋውያን*** – ይህ መጽሐፍ ራሱ ሕጎችን ይመለከታል። የሚተነትነውም የማደሪያው ድንኳን ከተሰራ እና በዘፀአት ውስጥ ክህነት ከተቋቋመ በኋላ ያለውን ሁኔታ ነው። የተጻፈውም እሥራኤላውያን በሲና ትራራ በነበሩበት ወቅት ነው (**ዘሌዋውያን 25፡1፣ 26፡46፣ እና 27፡34** ይመልከቱ)። ስለዚህ ጊዜው ከምድረ በዳው 40 አመታት በፊት ነው ማለት ነው፣ ስለዚህም ጊዜ በዘኍልቁ መጽሐፍ ውስጥ ተዘርዝሯል።

***ኦሪት ዘኍልቊ*** – ይህ በምድረ ባዳ የነበረው የ40 ዓምታቱ ጊዜ ዝርዝር ሁኔታ ነው የሚናገረው።

***ኦሪት ዘዳግም*** – ይህ ሙሴ ከመሞቱ በፊት እና እሥራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ወደ ተስፍይቱ ምድር ከመግባታቸው በፊት በሙሴ የተሰበኩ በሦስት ስብከቶች ላይ የሚያቶኩር ነው።





ሕጉ


## 3. የሕጉ ደራሲና አርታኢ


ሙሴ የሕጉ ጸሐፊ ነው (ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘጸአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቁ እና ኦሪት ዘዳግም)። ደግሞም ሙሴ መዝሙር 90ንም ጽፏል። ይህን ባለ አምስት ክፍል የሕጉ መጽሐፍ የጻፈው እሥራኤላውያን ቀይ ባሕርን ከተሻገሩ በኋላ በምድረ በዳ ሲቅበዘበዙ ሳይሆን አይቀርም። ሙሴ የእምነት ሰው ነበር (**ዕብራውያን 11:23–28** ይመልከቱ)። ደግሞም ስለ ክርስቶስ መምጣት ያውቅ ነበር፣ ስለዚህም ስለ እርሱ ጻፈ፣ እናም በመምጣቱ በማመኑም የመከራን ሕይወት መረጠ (**ዮሐንስ 1:45፣ 1 ጴጥሮስ 1:10–12 እና ዕብራውያን 11:23–28** ይመልከቱ)። በ 1 ጴጥሮስ 1:10–12 በተጻፈው መሠረት ደግሞ ሙሴ ጽሑፎቹን በኋለኞቹ ትውልዶች ዘንድ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለመርዳትና ወደ ክርስቶስም ለመምራት እንደሚጠቀሙባቸው ያውቅ ነበር።

የሙሴ ጽሑፎች ከእግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጠ ስጦታ ነው (**ዕዝራ 7:6** ይመልከቱ)። ጸሐፊው ሙሴ መሆኑን በብሉይ ኪዳን ግልጽ ነው (**1 ነገሥት 2:3፣ 2 ነገሥት 14:6፣ 2 ዜና 8:13፣ 23:18፣ 25:4፣ 34:14፣ 35:12፤ ዕዝራ 6:18፣ 7:6፤ ነህሚያ 1:8–9፣ 13:1** እና **ዳንኤል 9:11፣ 13**) እና ከአዲስ ኪዳን ደግሞ (**ማቴዎስ 19:7፣ 22:24፤ ማርቆስ 1:44፣ 7:10፤ ሉቃስ 16:29፣ 31፣ 20:37፣ 24:44፤ ዮሐንስ 1:17፣ 45፣ 5:45–46፣ 7:19–23፣ 8:5 ፣ 9:28–29፤ የሐዋሪያት ሥራ 3:22፣ 15:21፣ 26:22፣ 28:23፤ 2 ቆሮንቶስ 3:15** እና **ዕብራውያን 7:14** ይመልከቱ)። ሕጉ አንዳንድ ጊዜ "የሙሴ መጽሐፍ" ተብሎ ይጠራል (**ነህምያ 13:1** ይመልከቱ)።

ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ሙሴ የሕጉ ጸሐፊ ተደርጎ መወሰድ ያለበት ቢሆንም ቅሉ በሕጉ ውስጥ ያለውን ቃል ሁሉ አልጻፈም። ለምሳሌ **ዘዳግም 33**ን ሙሴ አልጻፈውም፤ ምክንያቱም **ዘዳግም 33:1** ስለ ሞቱ  ይናገራልና። በተጨማሪም **ዘዳግም 34** ስለ ሙሴ ሞት ይናገራል። እንግዲህ እነዚህን ቃላት መጻፍ አይችልም ነበር። ይህም የአርታዒው ቃል በህጉ ውስጥ እንደተካተተ የሚያሳይ ማስረጃ ነው። (በተጨማሪም በ**ዘፍጥረት 12:6፣ 13:7 እና 36:31** ላይ ያለውን የአርታዒውን ማብራሪያ ይመልከቱ)። ይህ አርታዒ እንደ ሙሴም በእግዚአብሔር መንፈስ የተነካ የእምነት ሰው ነበር። እንደ ሙሴም ደግሞ ክርስቶስን ይጠባበቅ ነበር። አርታዒው የጻፈው ሙሴ ከሞተ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው። በ**ዘዳግም 34:10** መሠረት ከሙሴ በኋላ የመጡትን የእሥራኤልን ነቢያት በጥንቃቄ ከመረመረ በኋላ አንዳቸውም እንደ ሙሴ እንዳልሆኑ ተናግሯል፤ ምክንያቱም አንዳቸውም እግዚአብሔርን እንደ ሙሴ ፊት ለፊት ስለማያውቁ

ነው። አርታዒው ነቢዩ ሙሴ በ**ዘዳግም 18፡15–19** የተናገረውን እየጠበቀ የነበረ ይመስላል። ይህም ስለሚመጣው ስለሌላ ነቢይ የተነገረ ትንቢት ነው። አርዒታው ቃሎቹን በሕጉ የመጨራሻ ምዕራፍ ላይ ሲጽፍ ያ ነቢይ ገና እንዳልመጣ አንባቢዎቹ እንዲያስተውሉ የሚፈልግ ይመስላል። አርታዒው የእምነት ሰው ነው! እግዚአብሔርን ፊት ለፊት የሚያውቅ ነቢይ እንዲጠብቁ እያሳሰበ ነው! ኢየሱስ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እየተነገረ የነበረው ነቢይ ነው (**ዮሐንስ 1፡17–18** እና **የሐዋሪያት ሥራ 3፡22–23** ይመልከቱ)።





### 4. ሙሴ የዘር ሐረግን በመጠቀም የኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍን እንዴት እንደከፋፈለው

ሙሴ ኦሪት ዘፍጥረትን ሲጽፍ በመዕራፍ ቁጥሮች (ወይም በጥቅስ ቁጥሮች) አልከፋፈለውም። ነገር ግን ምዕራፍና ቀጥሮች የተጨመሩት ኦሪት ዘፍጥረት ከተጻፈ ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ ነው። ይለቁንም ሙሴ **የትውልድ ሐረግ** በመጠቀም ኦሪት ዘፍጥረትን ከፋፍሏል። ሙሴ ለመጀመሪያ ጊዜ የትውልድ ሐረግን መጠቀም የጀመረው በ**ዘፍጥረት 2፡4** ላይ “እግዚአብሔር አምላክ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ የተከናወኑት እንደዚህ ነበር” ይላል። ሙሴ የትውልድ ሐረግን በዚህ ቦታ በማስገባቱ በመጽሐፉ ውስጥ አዲስ “ምዕራፍ” መጀመሩን ያሳያል። በተለይም ይህ ምዕራፍ ስለ ሰማያትና ምድር” ይናገራል። **ዘፍጥረት 1፡1–2፡3** የሙሴ መግቢያ ነው። የመጀመሪያው “ምዕራፍ” የሚጀምረው በ**ዘፍጥረት 2፡4** ላይ ሲሆን፤ የሙሴ የትውልድ ሐረግ ደግሞ በ**ዘፍጥረት 5፡1** ውስጥ ያስገባል።ይህም በዘፍጥረት ውስጥ አዲስ “ምዕራፍ” ይጀምራል ማለት ነው። ይህ “ምዕራፍ” ደግሞ በ**ዘፍጥረት 6፡8** ላይ ያበቃል። ይህም ግልጽ የሆነው ሙሴ አዲስ “ምዕራፍ” በ**ዘፍጥረት 6፡9** የጀመረ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም **ዘፍጥረት 10፡1፣ 11፡10፣ 11፡27፣ 25፡12፣ 25፡19፣ 36፡1፣** እና **37፡2** ይመልከቱ።



## 5. ቀደምት ክስተቶች አንባቢዎችን ለቀጣይ ክስተቶች ያዘጋጃሉ

በሕጉ ውስጥ የተገለጹት አብዛኞቹ ክንውኖች ጥቂት ሰዎችን ብቻ የሚያካትቱ ናቸው። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ እንዚህን ትናንሽ ክስተቶች በኋለኞቹ ክስትቶች ብዙ ተጨማሪ ሰዎችን በማሳተፍ ይባዛሉ። ይህም የኋለኛው ክንውኖች **ጥላ** የሆነው በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ነው። አንዱ ክስተት እየመጣ ያለውን ስለሌላኛው ክስተት ትንሽ ምስል ነው። ሙሴ ክስተቶቹን ለመግለጽ **ተመሳሳይ ቃላቶችን** ስለሚጠቀም አንባቢዎቹ በክስተቶች መካከል ያለውን ግኑኝነት እንዲረዱ እንደሚፈልግ በግልጽ የተናገር መሆኑን ያሳያል። ለምሳሌ ያህል **በረሃብ** ምክንያት አብርሃም ወደ **ግብፅ** እንደ ተጓዘ እንመለከታለን። በዚያም የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን የአብርሃምን ሚስት የመውሰድ ፍላጎት ነበረው፤ ያ ሂደት የተሳካ ቢሆን ኖሮ በአብርሃም በኩል የራሱን ሕዝብ የመገንባት የእግዚአብሔር እቅድ ያበቃለት ነበር። ነገር ግን ይህ እንዳይሆን **እግዚአብሔር በፈርዖንና በሕዝቡ ላይ መቅሰፍትን አወረደ፤ ስለዚህ ፈርዖን አብርሃምን ከግብፅ እንዲወጣ አደረገው**። አብርሃምም ከብዙ **ሀብት** ጋር ግብፅን ለቆ ወጣ እና (**ዘፍጥረት 12፡10–13፡1** ይመልከቱ)። እንግዲህ አብርሃም በግብፅ ያጋጠመው እና ከግብፅ መወጣቱ፤ በኋላ የእሥራኤል ሕዝብ ከግብፅ ነፃ ሲወጡ ምን እንደሚፈጠር የሚያሳዩ ትናንሽ ሥዕሎች ነበሩ (**ዘፀአት 1–14** ይመልከቱ)። ደግሞም እሥራኤላውያን ያጋጠማቸው ከግብፅ የመውጣት ክስተት ምንም እንኳን ብዙ ሰዎችን ያሳተፈ ቢሆንም በክርስቶስ ሥራ ምክንያት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከዓለም የሚሰበሰብበት ፍልሰት ሂደት ምሳሌ ወይም ጥላ ሲሆን ይህም እጅግ የሚበልጥ ፍልሰት እንደሆነ ያመለክታል (**ኢሳይያስ 11፡10–12:6** እና **ኤርሚያስ 23፡1–8** ይመልከቱ)።

እንደነዚህ አይነቱ ብዙ በዙ ክስተቶች በሙሴ መጽሐፍት ውስጥ አሉ። እነዚህ ቀደምት ክስተቶች ደግሞ ለዚህ ዘመን ለእግዚአብሔር ሕዝብ ትልቅ ዋጋ ያላቸው ናቸው። የቀደሙት ክንውኖች የእግዚአብሔር ሰዎች ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር ሲመለከቱ **እምነትን ለማጠንከር የሚጠቅሙ** ናቸው። በሕጉ በተገለጹት ቀደምት ክንውኖች ውስጥ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳዳነ ሁሉ፣ በኋለኞችም ቅዱሳት መጽሐፍት በተገለጹት የመጨረሻ ክንውኖችም ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚያደናቸው ጥርጥር የለውም።


ዘፍጥረት 1–11
ዘፍጥረት 12–50
ዘፀአት – ዘዳግም
የሙሴ መጽሐፍ

## 6. መግቢያ ሁለት የሕይወት ታሪኮችን በማስከተል

የሙሴ መጽሐፍ፣ በአንዳንድ መንገዶች፣ በሁለት ግለሰቦች መካከል ያለ ንጽጽር እንደሆነ ይገመታል፤ በአብርሃምና በሙሴ። ለዚህም ነው ከግለሰቦች ጋር የተያያዙ ጽሑፎች የሕይወት ታሪክ የሚባለው። ስለዚህም የሙሴ መጽሐፍ **ሁለት የሕይወት ታሪኮች** ያሉት መጽሐፍ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። መጽሐፉ ሆን ተብሎ የተጻፈው አንባቢው የእነዚህን ሁለት ሰዎች ሕይወት በማነፃፀር እሱ ወይም እሷ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ወሳኔዎችን እንዲውሰኑ ነው።


ዘፍጥረት 1–11 ለእነዚህ ሁለት የሕይወት ታሪኮች **መግቢያ** ሆኖ ያገለግላል። እነዚህ ምዕራፎች ደግሞ ስለ አንድ ሰው ብቻ አይደለም የሚተርኩት። ይልቁንም በእነዚህ ምዕራፎች ስለ መላው አለም ነው የተተረከው። እንግዲህ ይህ መግቢያ የሚያሳየው በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ሁለቱ ዋና ዋና የሕይወት ታሪኮች ለዓለም ሁሉ ጠቃሚ መሆናቸውን ነው። እግዚአብሔር የእሥራኤላውያን አምላክ ብቻ አይደለም። ነገር ግን እርሱ የሁሉም ሕዝቦች አምላክ ነው እንጂ።


ዘፍጥረት 12–50 ስለ አብርሃምና ስለ የቅርብ ቤተሰቡ የሚመለከት ነው። ይህም የተገለጸው ዘፍጥረት 12 በአብርሃም ጥሪ ሲጀምር እና ዘፍጥረት 50 ደግሞ የሚያበቃው ከአብርሃም የልጅ ልጆች አንዱ በሆነው በዮሴፍ ሞት ላይ ነው። ከዘጸአት አንስቶ እስከ ዘዳግም ድረስ ከሙሴ ጋር የተያያዘ ነው። ይህም የተገለጸው በዘጸአት ከሙሴ ልደት ጀምሮ ሲሆን በዘዳግም ደግሞ በሞቱ ያበቃል። በዚህ መንገድ ስንመለከተው የሙሴ መጽሐፍ ከሕይወት ታሪክ ጋር ይመሳሰላል።

**የሕይወት ታሪክ 1** – አብርሃም **ከእምነት** ጋር የተያያዘ ነው። የኖረውም ሕጉ ከመሰጠቱም በፊት ነው፤ ይሁን እንጂ ሙሴ አብርሃም ሕጉን የሚጥብቅ እንደ ነበር አድርጎ ገልጾታል ( ዘፍጥረት 26፡5 ይመልከቱ)። ኢየሱስ ደግሞ የአብርሃም ወራሽ ተብሎ ተጠርቷል (ማቴዎስ 1፡1 ይመልከቱ)። እንግዲህ ኢየሱስ "የአብርሃም ልጅ" ተብሎ የተጥራውም ለዚህ ነው። እንደዚሁም ደግሞ ክርስቲያኖች "በክርስቶስ" ስለሆኑ "የአብርሃም ልጆች" ተብሎው ተጠርተዋል (ገላትያ 3፡9፣ 14፣ 29)።

**የሕይወት ታሪክ 2** – ሙሴ **ከሕግ** ጋር የተያያዘ ነው፤ ይሁን እንጂ  እርሱ በብዙ መንገድ በሕይወት ከኖሩት ታላላቅ ሰዎች አንዱ ሆኖ ሳለ ሙሴ ግን ሕጉን መጠበቅ አልቻለም። በዚህም ምክንያት ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲገባ አልተፈቀደለትም። ስለዚህ የሙሴ ሕይወት በሕጉ መሠረት ለመኖር ለሚጥሩ ሁሉ ጥሩ ምሳሌ ነው (ገላትያ 3፡ 10–14 ይመልከቱ)።

ሙሴ ሰዎች በሕግ ሥራ እንደማይድኑ እና ከእግዚአብሔር መዳን በሌላ መንገድ እንደ ሚያስፈልጋቸው ያውቅ ነበር። እንደዚሁም ደግሞ የጻፈው መጽሐፍ የእግዚአብሔር ሕግ መሆኑን ቢያውቅም ነገር ግን ሰዎች እምነታቸውን በእነዚህ ሕጎች ላይ እንዲያደርጉ አልጻፈም። ይልቁንም፣ ሆን ብሎ መጽሐፉ የጻፈው “ከሕግ ውጭ” በሆነው በእግዚአብሔር ማዳን ላይ እምነት እንደሚያስፈልግ ለማሳየት ነው (ዛዳግም 4፡25–31፣ 30፡1–10 ይመልከቱ)።





## 7. ሙሴ ትረካዎችን እና ግጥሞችን እንዴት እንዳዋሃደ።


በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ **ትረካዎች** (ማለትም ብዙ ታሪኮች) አሉ (ለምሳሌ፣ ዘፍጥረት 4፡1–22 ይመልከቱ)። በሙሴ መጽሐፍ ውስጥም ደግሞ ብዙ **ግጥሞች** አሉ ( ለምሳሌ ዘፍጥረት 4፡23–24 ይመልከቱ)። ሰዎች በተለምዶ **ትረካ** ከመረዳት ይልቅ **ግጥሞችን** ለመረዳት ይታገላሉ። ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት **ግጥም ከፍ ያል ንግግር** ስለሆነ ነው። ይሁን እንጂ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ግጥም አይጠቀሙም። ይህ ማለት ደግሞ ምናልባት እንደ ሙሴ መጽሐፍ ባሉት መጻሕፍትም ውስጥ ቅኔ እንዴት "እንደሚሰራ" ሰዎች ላይረዱ ይችላሉ። ከዚህ ወጪ፣ ግጥሞች ብዙ የአነጋገር ዘይቤዎችን ይጠቀማሉ (ማለትም፣ ዘይቤዎችና ምሳሌዎች)። ግጥሞች እንግዳ በሆኑ ዘዴዎች ተደርድረዋል። እናም፣ ደራሲው የግጥሞቹን ዋና ነጥብ አላብራራም። ይልቁንም ድራሲው የግጥሙን ትርጉም አንባቢው በራሱ እንዲገነዘብ የፈለገ ይመስላል። እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ግጥሞችን ችላ ለማለት ቀላል ያደርጉለታል ማለት ነው። **ነገር ግን አንባቢ መጽሐፍ ቅዱሰዊ ግጥሞችን ችላ ማለት የለበትም። ምክንያቱም የሙሴ ስልቶች በጣም አስፈላጊ ክፍሎች ናቸውና።**

**ብዙ ጊዜ ሙሴ ትረካዎችን በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ካሉ ግጥሞች ጋር ያጣምራል። ሙሴ እነዚህን ሁለት የተለያዩ ነገሮች በአንድ ላይ በማጣመር አንድ ዋና ሃሳብ ላይ አፅናዖት ይሰጣል።** ሙሴ በአንድ በተለየ ክፍል፣በተለምዶ በትረካ ይጀምራል። በትረካው መጨረሻ ደግሞ ግጥም ያስገባል። በግጥሙና በትረካው መካከል ያለውን ትስስር ለማየት ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ቢሆንም አንባቢው ግጥሙ በሆነ መንገድ ከትረካው ጋር የተያያዘ መሆኑን ተረድቶ ወደፊት መቀጠል ይችላል። እንግዲህ ሙሴ እነዚህን ሁለት በጣም የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች በአንድ ላይ እንዲመረመሩ ያሰበ ይመስላል።

ሌላው ደግሞ፣ ከግጥሙ በኋላ ሙሴ ብዙ ጊዜ ግጥማአዊ ያልሆነ አጭር መደመደሚያ ያክላል። ይህም መደምደሚያ ከክፍሉ ጋር የተያያዙ የመጨረሻ አስተያየቶችን ያካትታል። ትረካዎቹ ለአንባቢያው የሚያስፈልገውን ዋና መረጃ የሚያቀርብ ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ ግን፣ የአንድ የተወሰነ ክፍል ዋና ነጥብ በግጥሙ ወይም በመደምደሚያው ውስጥ ይገኛል። እነዚህ የማጠቃለያ ሀሳቦች ደግሞ ልክ እንደ ግጥሞቹ ከትረካዎቹ ያነሱ ናቸው። እንግዲህ ሙሴ እነዚህን ሶስት አካላት ማለትም ( ትረካዎችን፣ ግጥሞችን እና የመደምደሚያ ሀሳቦችን) በአንድ ላይ በማጣመር ነው በመጽሐፉ ውስጥ ለተለያዩ **"ክፍሎች" ወሰኖችን** ያደረገው። ይህ በእንዲህ እንዳለ የመደምደሚያው ሀሳብ የሙሴን መጽሐፍ የያዘ የተወሰነ "ክፍል" መጨረሻን የሚያመለክት ሲሆን፣ ደግሞም አንባቢውን በመጽሐፉ ውስጥ ለሚቀጥለው ክፍል ያዘጋጀዋል ማለት ነው።

ለምሳሌ፣ ዘፍጥረት 4 በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ አዲስ "ክፍል" ነው። ይህም "ክፍል" በአዳምና በሔዋን ልጆች ላይ ያተኮረ ነው። ይህ ክፍል ደግሞ የሚከናወነው ከኤደን ገነት ውጪ ነው። በዘፍጥረት 4፡1–22 ሙሴ ስለ ቃየንና ስለ አቤል መወለድ፣ እንደዚሁም ቃየን አቤልን እንዴት እንደ ገደለው ይተርካል። እግዚአብሔር ደግሞ ቃየንን ፊት ለፊት እንደ ተከራከረው፣ እንድዚሁም ቃየን በምድር ላይ መንከራተቱን እና ስለ ቃየን ክፉዎች ዘሮቹ ይተነተናል። **ከቁጥር 1–22 ያሉትን ቁጥሮች ሁሉም ትረካዎች** ናቸው። ነገር ግን እነዚህ ስለ ቃየንና ስለዘሮቹ የተነገሩ ታሪኮች ያልተሟሉ ናቸው! ግጥሙና ማጠቃለያው ከሌለ አንባቢ በዚህ የትረካ ክፍል ብቻ ሙሴ የሚያጎላበትን ነጥብ ምን እንደሆነ ለመረዳት ሊቸገር ይችላል። የሙሴ ቁም ነገር፣ የሰው ልጅ ፍፁም አምላክ የለሽ እና ክፉ ሆኗል፣ እናም ይህንን ችግር ለመቀረፍ ደግሞ አዳኝ ያስፈልገዋል የሚል ነው። **የሰው ልጅ የክፋት ደረጃ ምን ያህል እንደ ደረሰ ከቁጥር 23–24 ባለው ግጥም ላይ ጎልቶ ይታያል። ይህ ግጥም የተጻፈው ከክፉ ሰው አመለካከት አንፃር ነው። ግጥሙም በሞት መደሰትን ያሳያል። ሙሴ ይህንን ግጥም ያካተተው ሰዎች ምን ያህል ክፉ መሆናቸውን ለማሳየት ይመስላል። እንደዚሁም አንባቢው በስሜቱ እንዲገነዘብ የተተወ ደግሞ ይመስላል፣ ማለትም አዳኙ በተሎ የማይመጣ ከሆነ ለሰዎች የሚሆን ምንም አይነት ተስፍ ላይቀር ይችላል የሚል እንድምታ ያለው ይመስላል። በዚህ ላይ ደግሞ ግጥሙ ያልተሟላ ግጥም ነው። ስለዚህ የትረካው መልዕክት የበለጥ እንዲብራራ መደምደሚያ አስተያየቶች ያስፈልጋሉ ማለት ነው።** በመጨረሻም፣ **ዘፍጥረት 4** የሚደመደመው የሴትን መወለድ በሚገልጹ በሁለት ጥቅሶች ነው። ሔዋን ደግሞ ሴትን "ሌላ ዘር" እንደ ሆነ ተናገረች። እንግዲህ በ**ዘፍጥረት 3፡15** ባለው የእግዚአብሔር ቃል በመመስረት፣ ይህ ማለት ሔዋን ሴትን በዓለም ላይ ላለው የክፉት ችግር እንደ መልስ ተመልክታው ሊሆን ይችላል። ሴት እንግዲህ እባቡን ለማሸነፍ ሚና የሚጫወተው ዘር ነውና! ይህ ክፍል የሚደመድመው "በዚያም ዘመን ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ጀመሩ" በሚሉ ቃላቶችን ነው። እነዚህ የማጠቃለያ አስተያይቶች በጣም ጠቃሚ ናቸው፣ ምክንያቱም አንባቢው የዚህን ዋና ክፍል ነጥብ እንዲገነዘብ ይረዱታልና። በኃጥያት ምክንያት የአምልኮ ጉድለት ስለነበር፣ እግዚአብሔር እንዲመለክ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ዘር መምጣት ያስፈልግ ነበርና።

እንዲህ አይነቱ አገላለጽ በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግሞ ይታያል። እንዲህ አይነቱ ክስተት ደግሞ በግለሰቦች ታሪክም ትንተና ውስጥ ይታያል (እንደ **ዘፍጥረት 4**) እንደዚሁም ደግሞ በትልልቅ “የክስተቶች ስበስብ” ውስጥም ይታያል (ለምሳሌ፣ በ**ዘፍጥረት 49** ላይ የአብርሃምን የቤተሰብ ታሪክ በሚዘረዝረው ከረጅም ትረካ በመቀጠል በጣም ትልቅ ግጥም እናገኛለን)።



## 8. ሙሴ ትረካዎችንና ሕጎችን እንዴት እንዳዋሃደ

ሙሴ ትረካዎችን እና ግጥሞችን እንዳዋሃደ ሁሉ **ትረካዎችን ከሕግ** (ወይም መመሪያዎች) ጋር አጣምሯል። ሕጎችና መመሪያዎች ከየትኛውም ቦታ ውጪ የሚታዩ እንግዳ ሕጎች አይደሉም። ነገር ግን እነዚህ ሕጎች ከተከናወኑ ክስተቶች ጋር የተገናኙ ሲሆኑ ተረቶቹና ሕጎቹም (ወይም መመሪያዎቹ) አብረው እንዲነበቡ የታሰቡ ናቸው። ትረካዎችና ሕጎች ሲያያዙ በተለምዶ ሕጎቹ ከትረካዎቹ በኋላ ይከተላሉ እና ሕጎቹ ደግሞ ከትረካዎቹ የበለጠ ቦታ ይወስዳሉ። ለምሳሌ፣ **ዘፀአት 33–34** ከወርቅ ጥጃ ክስተት በኋላ የተከናወኑ ድርጊቶችን የሚገልጽ ትረካ ነው። እንግዲህ በሲና ተራራ የተድረገው ይህ ታላቅ ኃጢአት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለውን ግኑኝነት እንዲለወጥ አድርግታል። ስለዚህ በ**ዘፀአት 33–34** ሙሴ አዲስ የድንጋይ ጽላቶች ተሰጥቶት ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን ተመሠረተ። እነዚህ ሁለት የትረካ ምዕራፎች ከማደሪያው ድንኳንና ከካህናት እና ከመሥዋዕቶች ጋር የተያያዙ ሕጎች እና መመሪያዎች ዝርዝር ይከተላሉ። እንግዲህ ሕጎቹና መመሪያዎች የሚጀምሩት በ**ዘፀአት 35** ነው፤ (በ**ዘፀአት 35፡1** ላይ ያለውን የሙሴን ቃል ይመልከቱ) ከዚያም በመላው ዘሌዋውያን መጽሐፍ ይቀጥላል። እንደዚሁም ደግሞ በ**ዘፀአት 35** እና በ**ዜሌዋውያን 27** መካከል ያሉትን ሕጎችና መመሪያዎች በዘፀአት 33–34 ካለው ትረካ ጋር እንደተገናኙ መታየት አላባቸው። የዘሌዋውያንን የመጨረሻ ቃል እስቲ ልብ ብለው ይመልከቱ፡– “እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በሙሴ አማካይነት ለእሥራኤል ሕዝብ የሰጣቸው ትእዛዝ እነዚህ ናቸው” ይላል። ይህ ጥቅስ በ**ዘፀአት 33–34** ውስጥ ካሉት ክንውኖች ጋር ለተያያዙ ሕጎችና መመሪያዎች መደምደሚያ ሆኖ ያገለግላል ማለት ነው።



## 9. በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ማዕከላዊ ክንውኖች


የሙሴ መጽሐፍ በአምስት ክፍሎች የተከፈለ ቢሆንም (ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም) እንደ አንድ ትልቅ መጽሐፍ ሊወሰድ እንደሚችል ብዙ ማሳያዎች አሉ። አንዱ ማሳያ በኋለኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች "የሙሴ **መጽሐፍ**" ተብሎ መጠቀሱ ነው (ማርቆስ 12 ፡26 ይመልከቱ)። በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ አለም አቀፍዊ ጠቀሜታ ያላቸው ብዙ ክስተቶች አሉ (እነዚህም፤ ፍጥረት፣ ጎርፍ፣ የባቢሎን ግንብ፣ የአብርሃም ጥሪ፣ ዘፀአት፣ ወዘተ፣ ወዘተ . . . )። ሆኖም እነዚህ ሁሉም ጉልህ ክንውኖች ቢሆኑም፣ በዚህ ትልቅ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት እውነቶች ሁሉ ግን አንድ ክስተት ጎልቶ **ቀርቧል**። እንግዲህ ደራሲው አንባቢዎቹ ከሌሎቹ ሁሉ በላይ እንዲያዩት የሚፈልገው ይህ ክስተት ምንድር ነው? ይህም በሲና ተራራ ላይ በተሰጠው ቃል ኪዳን ውስጥ የሚገኝ ክስተት ነው።

በብዙ ነገሮች ላይ በመመስረት (ማለትም፣ ለዚህ ክስተት የተሰጠው የቦታ መጠን፣ በቁጥቋጦ እሳት ውስጥ በተገለጠበት ጊዜ) እግዚአብሔር ለሙሴ የተናገረው ቃል፣ ወዘተ) ደራሲው (ሙሴ) አንባቢው ይህንን ክስተት እንደ ትልቅ ትርጉም እንዲያየው እንደሚፈልግ ግልጽ ነው። ከሁለቱም የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ማለትም (ነቢያትና ጽሑፎች) በኋላ የተጻፉት ጽሑፎች በሲና ተራራ ላይ በተፈጸሙ ድርጊቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ደራሲው እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን የተስፋ ቃል ፍጻሜ የሚያመጣበትን መንገድ በሲና ተራራ ላይ የተናገረውን ቃል ኪዳን አቅርቧል (ዘፍጥረት 12፡1–3 ይመልከቱ) እና ለምድርም በረከትን አመጣ። በሲና ተራራ ላይ፣ እግዚአብሔር በራሱና በእሥራኤል መካከል ቃል ኪዳንን አቆመ። እዚህ ጋ እግዚአብሔር ለእሥራኤል ቃል ኪዳን ገብቷል፤ ይህም ቃልኪዳን መላውን ዓለም የሚነካ ቃል ኪዳን ነው። እሥራኤልም ደግሞ የተጠራችው ቃል ኪድኑን እንድትታዘዝ ነው።

ነገር ግን በሲና ተራራ የተሰጠው ቃል ኪዳን በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ **ከተገለጹት ክንውኖች ሁሉ በላይ ጎልቶ የሚታየው ክስተት** ቢሆንም ቅሉ ሙሴ አንባቢው የሲና ተራራን የእግዚአብሔር ተስፋዎች ፍጻሜ አድርጎ እንዲያየው ይፈልጋል ማለት አይደለም፣ እንደዚሁም ደግሞ አንባቢዎቹ በሲና ተራራ በተሰጠው ቃል ኪዳን ላይ እምነት እንዲኖራቸው ይፈልጋል ማለትም አይደለም። ነገር ግን ሙሴ አንባቢዎቹን በሲና ተራራ ላይ ካለው ቃል ኪዳን ባሻገር እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርገውን አዲስ ነገር እንዲመለከቱ በግልጽ ይፈልጋል። (**አዲስ ኪዳን** የሚሉት  ቃላቶች በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ጥቅም ላይ አልዋሉም። ነገር ግን በኋለኞቹ መጻሕፍት በብሉይ ኪዳን እንዲሁም በአዲስ ኪዳንም ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል)።

ሙሴ እሥራኤላውያን ለቃል ኪዳኑ አለመታዘዛቸውን በግልፅ አሳይቷል፤ ስለዚህ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲገቡ ቃል ኪዳኑን መጠበቅ እንደማይችሉ ደግሞ ተናግሮ ነበር። ይህ ማለት ግን ሙሴ አንባቢው የእግዚአብሔርን አላማዎች እንደማይፈጸሙ እንዲያስብ ይፈልጋል ማለት አይደለም። ይልቁንም ጸሐፊው የእግዚአብሔር ዕቅዶች በሲና ተራራ በተገለጠው መንገድ እንደማይፈጸሙ አንባቢዎቹ እንዲገነዘቡ ይፈልጋል። እንደዚሁም ሙሴ መጽሐፉን የሚያነቡ ሰዎች እግዚአብሔር ወደፊት በሚያደርጋቸው ነገሮች ላይ እምነት እንዲኖራቸው ይፈልጋል። ምክንያቱም እሥራኤላውያን በሲና ተራራ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን መጠበቅ አልወደዱምም አልቻሉምም።






## 10. የእግዚአብሔር መልካም ፍጥረት


በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ (**ዘፍጥረት 1፡1፣ ሮሜ 11፡36፣ ራዕይ 4፡11** ይመልከቱ)። ይህ ማለት ደግሞ እግዚአብሔር የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ ፈጠረ ማለት ነው። አጽናፈ ሰማይ እና በአጽናፈ ሰማይ ውስጥ ያሉትን ነገሮች በድንገት የሆኑ ነገሮች አይደሉም፤ እንደዚሁም አጽናፈ ሰማይና በአጽናፈ ሰማይ ውስጥ ያሉትን ነግሮች በዝግመተ ለውጥ የተገኙም አይደሉም። አጽናፈ ሰማይ እና በውስጡ ያለው ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተገለጸው መንገድ በእግዚአብሔር ሆን ተብሎ የተፈጠረ ነው። ምድር የተፈጠረው ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ ብቻ እንዲሆን አልነበረም። **ነገር ግን ምድር የተፈጠረው እግዚአብሔርና ሰዎች በአንድነት የሚኖሩበት እና እግዚአብሔር ደግሞ የሚመለክበት ቦታ እንዲሆን ታስቦ ነው** (**1 ዜና 29፡11** ይመልከቱ)። እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው እርሱ የሚመለክበት "ትያትር" አድርጎ ነው። በሰማይና በምድር ያሉትን ሁሉ ውዳሴውን ያለማቋረጥ እንዲያውጁ ታቅዶ የተደረጉ ናቸው (**መዝሙር 148** እና **ዕንባቆም 3፡3** ይመልከቱ)። ደግሞ እግዚአብሔር እርሱ ብቻ ፈጣሪ እንደሆነ ያለማቋረጥ ይናገራል።

የአዳም ኃጢአት በሰዎች ብቻ ላይ አይደለም ተጸዕኖ ያሳደረው በእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ላይ ነው እንጂ፤ በዚህም ምክንያት የመጀምሪያው ሰማይና ምድር በእርግማን ውስጥ ይገኛሉ። ስለዚህ አንድ ቀን እንዲጠፉ ይደረጋል። ከዚያም የእግዚአብሔር ሕዝብ በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር ይኖራሉ (**ኢሳይያስ 24፡5–6፣ 65፡17፤ ሮሜ 8፤ 2 ጴጥሮስ 3፡1–13** እና **ራዕይ 21፡1** ይመልከቱ)።



## ll. በኤደን ውስጥ የነበረው የአትክልት ሥፍራ

መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው አዳም በመፈጠሩ እና በገነት ውስጥም በመቀመጡ ሂድት ላይ ነው (**ዘፍጥረት 2፡8** ይመልከቱ)። የአትክልት ስፍራው እግዚአብሔር የሚመለክበት ቤተ መቅድስ ነበር። አዳም ደግሞ ገነትን የመንከባከብ እና የአትክልት ስፍራውንም የመጠበቅ ሃላፊነት ተሰጥቶት ነበር (**ዘፍጥረት 2፡ 15** ይመልከቱ)። በአትክልቱ ውስጥም ከእርሱ ለበሉት ሁሉ የዘላልም ሕይወትን የሚሰጥ ዛፍ ነበረ። ነገር ግን አዳምና ሔዋን ከዚህ ዛፍ አልበሉም። ይልቁንም ሊበሉ ካልተፈቀደላቸው ዛፍ በሉ (**ዘፍጥረት 2፡16–17 እና 3፡1–7** ይመልከቱ)። በብዙ መንገድ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጭርሰው በጀመረው መንገድ ነው። የአትክልት ሥፍራ አለ እናም በውስጡ ደግሞ የሕይወት ዛፍ አለ። በመጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ ላይም የአትክልት ቦታው መላውን ምድር ሞልቶ እንመለከታለን! የሕይወት ዛፍም በወንዙ በግራና በቀኝ በኩል ይበቅላል። እንደዚሁም በመጽሕፍ ቅዱስ መጨረሻ ላይ ሰዎች ከሕይወት ዛፍ ይበላሉ! በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱት ብዙ ደራሲዎች ስለዚህ ዛፍ እና ወንዙን በተመለከተ ጽፈዋል (**መዝሙር 1፡3፤ ሕዝቅኤል 47፡12፤ ራዕይ 2፡7፣ 22፡1–5፣ 22፡19** ይመልከቱ)።



## 12. የመጀመሪያው “ንጉሥ” እና “ካህን” አለመታዘዝ

ምንም እንኳን አዳም ንጉሥ ቢሆንም እግዚአብሔር በፈጠረው ምድር ላይ ሥልጣን ቢሰጠውም ቅሉ (**ዘፍጥረት 1፥26** ይመልከቱ)፣ ገደብ የለሽ ሥልጣን የነበረው ንጉሥ አልነበረም። ይልቁንም በሌላ ገኹ ማለትም በእግዚአብሔር የሚመራ ንጉሥ ነበር። አዳም ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ህግጋት ሥር መኖር የነበረበት ንጉሥ ነበር። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሕጎች እንዲለውጥ እንዲሁም ትክክልና ስህተት የሆነውን ለራሱ እንዲውስን አልተፈቀደለትም ነበር። እባቡም ደግሞ በአዳም ፊንታ ሄዋንን በማናገር የእግዚአብሔርን ስልጣንና የአዳምን ቦታ እንደማያከበር አሳይቷል። እባቡ ሄዋንን እግዚአብሔርን እንዳትታዘዝ የዛፉንም ፍሬ እንድትበላ አሳመናት። ስለዚህ እባቡ ሄዋንን አሳታት። አዳምም ደግሞ ከእርስዋ ጋር ተባበረ። ነገር ግን እርሱ አልተታለለም ነበር፤ የዛፉንም ፍሬ መብላት እንደሌለበት ያውቅ ነበር። ይሁን እንጂ እርሱም በእግዚአብሔር ላይ አመጸ (**1 ጢሞቴዎስ 2፥13–14** ይመልከቱ)። እባቡ ሰይጣን እንደሆነ ተጽፏል (**ራዕይ 12** ይመልከቱ)። በኤደን ገነት ውስጥ በእባብ ተመስሎ ተገለጠ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው ታሪክ እየጨመረ በመሄድ ያድጋል፤ በዚሁ መሠረት በራዕይ ውስጥ ዘንዶ ተብሎ ተገልፆአልና።

የአዳም ኃጥያት በሰዎች ልጆች ሁሉ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል ምክንያቱም ሁሉም ሰዎች የአዳም ዘር ናቸውና። ይህ ማለት ደግሞ እያንዳንዱ ሰው ማለትም ወንድም ቢሆን ሴት ሁሉም የአዳም ዘር በመሆናቸው ምክንያት የአዳምን መንፈሳዊ ሁኔታ ይጋራሉ ማለት ነው። ስለዚህ አዳም ኃጢአትን ስለሠራ፣ ሰዎች ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል (**ሮሜ 1፥21–23፣ 3፥23** እና **5፥12፣19** ይመልከቱ)። ለዚህም ነው ኢየሱስ “ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ቸር የለም” ያለው (**ማርቆስ 10፥18** ይመልከቱ)። በአዲስ ኪዳን፣ ኢየሱስ እንደ “ኋለኛው አዳም” ተገልጿል (**1 ቆሮ 15፥45** ይመልከቱ)። በዚህም ምክናያት፣ “በክርስቶስ” ያሉት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ጻድቃን ተቆጥረዋል (**2 ቆሮንቶስ 5፥17፣ 21** ይመልከቱ)። ስለዚህ የዘላለም ሕይወትን ይወርሳሉ።




## 13. የኃጢአት ውጤቶች

አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው፣ እስከ ዛሬም ድረስ በሁሉም ሰዎች ላይ እየደረሰ ያለ አንድ አሰቃቂ ነገር ተፈጸመ። ሰዎች አሁንም ቢሆን የሚኖሩት ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ ነው። ኃጢአት ስንሠራ እግዚአብሔር ደስ አይለውም። የእግዚአብሔር ቃል መልካም ነው፤ አለመታዘዝ ግን ክፉ ነው። እግዚአብሔር ቃሉ ሲዋረድና ሳንታዘዘው ሲቀር ግድ ባይሰጠው ለቃሉ ደንታ እንደሌለው ያሳያል። ከራሱም በላይ ሌላ ነገር እንደ ሚያከብር ሊቆጠር ይችል ይሆናል። ስለዚህ እግዚአብሔር መልካም ነውና በኃጢያት አለመደሰቱን ማሳየት አለበት፤ በኃጢአት ላይ ካልፈረደ ለስሙና ለቃሉ ደንታ የለውም ማለት ነው። እስቲ በዚህ ሥፍራ የነፈሰውን ንፋስ ምሳሌ ይመልከቱ ፤ **ዘፍጥረት 3፡8** እግዚአብሔር "በቀን ንፋስ" ሊመላለስ እንደመጣ ይናገራል። ይህ ማለት ምናልባት ማዕበል መጣ ማለት ሊሆን ይችላል! ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚታይ ማዕበል ባይኖርም፤ የአዳም ኃጢአት ግን መንፈሳዊ ማዕበል ፈጥሮ ሊሆን ይችላል። በዚህ ማዕበል ውስጥ አዳም ሚስቱን እያጽናና እንዳልነበረ ግልጽ ነው። ይህም ሁኔታ በኃጢአት ምክንያት ሰዎች እርስ በርሳቸው እንደማይተሳሰቡ ያሳያል። ምክንያቱም ከእንግዲህ "አንድ ሥጋ" አይደሉም። ለዚህ ማስረጃ ደግሞ እግዚአብሔር አዳምን ስለ ኃጢአቱ ሲያናግረው በሚስቱ ሲያሳብብና እርሷንም ሲወቅስ እንመለከታለን። ይህ ብቻ አይደለም ሔዋንን ስለ ሰጠው እግዚአንብሔርንም ሲወቅስ እንመለከተዋለንና (**ዘፍጥረት 3፡12** ይመለከቱ)።



## 14. እግዚአብሔር አዳኝ እንደ ሚመጣ ተስፍ ሰጥቶ ነበር

በአዳም ኃጢአት ምክንያት፣ እባቡ በምድር ላይ ገዥ ሆነ! አዳምና ሔዋንም ከእግዚአብሔር ይልቅ እባቡን ታዘዙ (**ኤፌሶን 2:1–3** ይመልከቱ)። ምንም እንኳን ሰይጣን በምድር ላይ "ገዥ" ቢሆንም ነገር ግን በምድር ላይ ባለሙሉ ስልጣን "ገዥ" እንዳልሆነ ማወቁ ጠቃሚ ነው። እርሱ ከእግዚአብሔር በላይ አይደለምና፤ የእግዚአብሔርንም እቅዶች መለወጥ አይችልም። አዳም ቢበድልም እንኳን የአዳም በደል እግዚአብሔርን ሥፍራ አሳጥቶት አያውቅም። ነገር ግን ሰዎች ቦታቸውን አጥተዋል። እንደዚሁም ሰይጣን እግዚአብሔርን ይወድ ከነበረውና የእግዚአብሔርም "ልጅ" ሆኖ ይገዛ ከነበረው ሰው ይልቅ በምድር ላይ ገዥ ስለሆነ እውነተኛ የእግዚአብሔር አምልኮ አይፈጸምም ነበር። እግዚአብሔር ግን የእባቡን ራስ "የሚቀጠቅጥ" ሰው እንደሚመጣ ቃል ገብቶ ነበር (**ዘፍጥረት 3፡15** ይመልከቱ)። ይህም ክርስቶስ ሰይጣንን ድል አድርጎ እንደሚይዘው የሚያመለክት ተስፋ ነበር። እንደዚሁም ክርስቲያኖች ደግሞ "በክርስቶስ" ስላሉ፣ ሰይጣንን ድል ስለማድረጋቸው ጭምር ደግሞ የተነገረም ተስፋ ነው (**ሮሜ 16፡20** ይመልከቱ)።




## 15. የሴቲቱ ዘር እና የእባቡ ዘር

የስዕሉ ምሳሌ ሁለት ቡድኖችን ያሳያል። ሰዎቹ አንዳይነት ቢመስሉም ነገር ግን በሁለቱ ቡድኖች መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። አንደኛው ወገን ለእግዚአብሔር የተሰጠ ማንነት ያላቸው ሰዎችን ይወክላል። ሌላኛው ወገን ደግሞ ለሰይጣን ያድሩ ሰዎችን ይወክላል። በቡድኖቹ መካከል ያለውን ልዩነት ለመለየት እንዲያስችል አንዱ በቀይ ቀለም የተከበበ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በቢጫ ቀለም እንዲከበብ ተደርጓል። ይህ የሁለት የተለያዩ የሰዎች ቡድን ሃሳብ የመጣው በ**ዘፍጥረት 3፡15** ላይ እግዚአብሔር ለእባቡ ከተናገረው ቃል ነው፡– "በአንተና በሴቲቱ፣ በዘርህና በዘሯ ማካከል ጠላትነትን አድርጋልሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ።"

በዚህ ቃል፣በሴቲቱና በእባቡ ማካከል እንዲሁም በሴቲቱ ዘርና በእባቡ ዘር መካከል ስላላው ጥላቻ ያህዌ (እግዚአብሔር) ይናገራል። የሴቲቱ ዘር ክርስቶስ እና በእርሱ ውስጥ የተቆጠሩት ናቸው። የእባቡ ዘሮች አካላዊ እባቦች አይደሉም፤ ነገር ግን ክርስቶስና የክርስቶስ የሆኑትን ሁሉ የሚቃወሙ ሰዎች ናቸው እንጂ። በሁለቱም መካከል ያለው "ጦርነት" በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በብዛት ተገልፆአል። በመጀመሪያ የተነገረው በዘፍጥረት 3፡15 ሲሆን፤ ጦርነቱም በ**ዘፍጥረት 4** ላይ ይጀምራል! በዘፍጥረት 4 ከቃየን እና ከአቤል ጋር ተዋውቀናል። ሁለቱም ማለትም ቃየንና አቤል እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ይመስላሉ፣ ነገር ግን ቃየን እግዚአብሔርን የሚያመልክ ቢመስልም እንኳ፣ ቃየን ግን እግዚአብሔርን እንደ ማይወድ ግልጽ ነው። የእግዚአብሔርንም ቃል አይታዘዝም ነበር። እናቱ ሔዋን ስለሆነች ከእባቡ ጋር የሚዋጋው የእግዚአብሔራዊ ዘር አካል ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። ይልቁንም እሱ ሊመጡ ስለሉቱ ብዙ የእባቡ ዘሮች ከሚሆኑት እንደ መጀመሪያው መቆጠር ያለበት ሰው ነው (**1 ዮሐንስ 3፡12** ይመልከቱ)። ቃየን እንደ እባቡ ልጅ ነው የሰራውና የእባቡንም ፍላጎት ለማድረግ የፈለገው (**ዮሐንስ 8፡44** ይመልከቱ)። ነገር ግን አቤል ከቃየን የተለየ ነበር። በእውነትም እግዚአብሔርን ያመልክ ነበር። አቤል የእግዚአብሔር "ልጅ" ስለሆነ ፈቃዱን ለማደርግ ይፈልግ ነበር። በዚህ የመጀመሪያ ጦርነት አቤል ተሰደደ ከዚያም በቃየን ተገደለ። እዚህ ጋ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለውን ዘር ስለተገደለ የእባቡ ዘር ያሸነፈ ይመስላል። ሆኖም አቤል ምንም እንኳን ቢሞትም፣ እስከ መጨረሻው ግን አልተሸነፈም (**ዕብራውያን 11፡4** ይመልከቱ)። በምዕራፉ መጨረሻም ሔዋን በአቤል ምትክ ሌላ **ልጅ** አገኘች፤ ስሙም ሴት ተባለ። ሔዋን "ቃይን በገደለው በአቤል ፋንታ ምትክ ሰጠኝ ስትል ሴት ብላ ጠራቸው" (**ዘፍጥረት 4፡25** ይመልከቱ)። እንግዲህ ይህ በመጀመሪያ በዘፍጥረት 3፡15 የተገለፀው በሁለቱ ዘሮች መካከል የተደረገ የመጀመሪያው ጦርነት ነው።

ከዘፍጥረት 4 በኋላ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእነዚህን ሁለት የሰዎች ቡድኖች “መስመሮች” ይከተላል። የእባቡ ዘርም ጠንከር ያለ እና በመጨረሻም የሚያሸንፍ ቢመስልም፣ እውነታው ግን ይህ አይደለም። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር እርዳታ የተነሳ የሴቲቱ ዘር በእባቡ ዘር ላይ ያሸንፋል። ለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ፡– “የሰላም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል” ያለው (**ሮሜ 16፡20**)። እንግዲህ በዚህ አለም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የዚህ ግጭት አካል ናቸው ማለት ነው (**ኤፌሶን 2፡1–3** ይመልከቱ)።





## 16. ከእግዚአብሔር መልካም ከሆነው ቦታ ውጭ ያለው ችግር (እና ጸጋ)

አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር መልካም ቦታ እንዲቆዩ አልተፈቀደላቸውም። ከመልካሙ ሥፍራም መውጣት ነበረባቸው፤ ምክንያቱም ቢቆዩ ኖሮ በእግዚአብሔር ላይ ማመጻቸውን ይቀጥሉ ነበርና፤ እንደዚሁም ደግሞ ከሕይወት ዛፍም ለመብላት ይሞክሩ ነበር። በዚያን ጊዜ ከሕይወት ዛፍ በልተው ቢሆን ኖሮ ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነው ለዛላለም ይኖሩ ነበር (**ዘፍጥረት 3፥22** ይመልከቱ)። እግዚአብሔር አምላክ ካዘዛቸው ነገር ይልቅ በዓመፀኛ ተፈጥሮአቸው ምክንያት ይበጀናል ብለው ያሰቡትን ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት ልቆ ይታይ ነበርና፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ ሳያጠፋቸው ከገነት አባረራቸው። ከአትክልቱም ስፍራ ውጭ በሚቆዩበትም ጊዜ ቢሆን፣ ከነ ኃጢአታቸው ለዘላለም እንዳይኖሩና በምድረ በዳውም ለዘላለም እንዳይሆኑ አስፈላጊውን ሥራ ሲያከናውን ነበር። ነገር ግን ምንም እንኳን አሁን ከእግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ውጪ የሆኑና በምትኩም በምድረ ባዳ ውስጥ ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር አሁንም ጸጋውን ሰጣቸው። ይህም በስዕሉ ላይ የምትመለከቱት በቢጫው ቀለም ይመሰላል። በምድረባዳ ቢሆኑም እንኳን እግዚአብሔር ወደ መልካሙ ሥፍራ የሚመለሱበትን መንገድ አዘጋጀላቸው። ወደ መልካሙ ሥፍራ መመለሻው በቸኛው መንገድ ደግሞ በኢየሱስ በኩል ነው። እርሱም ሰዎች እንደገና ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው በእውነት እርሱን የሚያመልኩበት ምንገድ ነው (**ዮሐንስ 14፥1–6** ይመልከቱ)። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ያዘጋጀው የሕይወት መንገድ **ወንጌል** እንደሆነ ይናግራል። ወንጌል ደግሞ የክርስቶስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ **የምሥራች** ነው። ወንጌል እንደ ሚሰራ ደግሞ ግልጽ ነው ምክንያቱም የራዕይ መጽሐፍ እንደሚነግረን ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ የተወጣጡ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደ ሚያመልኩ ይናግራልና። እነዚህ ደግሞ ከእግዚአብሔር የሕይወት ዛፍ እንዲበሉ ተፈቅዶላቸዋል (**ራዕይ 22፥14** ይመልከቱ)።



## 17. ጥፋት እና መዳን

እግዚአብሔር ፈጣሪ ብቻ አይደለም (**ዘፍጥረት 1–2**)። ነገር ግን የፈጠረውንም ለማጥፋት ዝግጁ ነው (**ዘፍትረት 6–8**)። በሥዕሉ ላይ እንደ ምትመለከቱት፤ እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን በዓለምና በውስጥዋ በሚኖረው ሁሉ ላይ የጥፋት ፍርድ ለመፍረድ ፈቃደኛ እንደነበር ያሳያል። እግዚአብሔር ይህን ያደርገው በሰዎች ታላቅ ክፋት ምክንያት ነው (**ዘፍጥረት 6:5** ይመልከቱ)። እንዲህ አይነቱ ክስተት በመጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትናንሽ ጉዳዮች ሳይቀር ተከስቶ እንመለከታለን። በሎጥ ዘመንም የሶዶም ጥፋት መጥቀስ ይቻላል (**ዘፍጥረት 19** ይመልከቱ)። እንደዚሁም እግዚአብሔር በሙሴ ዘመን ግብፅን ባጠፋ ጊዜም ታይቷል። በተጨማሪም በሚያስገርም ሁኔታ ደግሞ እግዚአብሔር በሰዎች ኃጢአት ምክንያት በመስቀል ላይ ሲሞት በልጁ ላይ መአቱን ባፈሰሰ ጊዜም ታይቷል። በመጨረሻው ዘመንም ደግሞ እግዚአብሔር አሁን ያሉትን ሰማይና ምድርም ሲያጠፋ ይታያል (**2 ጴጥሮስ 3:1–13**).


ይሁን እንጂ የጥፋት ወኃው እግዚአብሔር ፍጥረቱን ለማጥፋት ፈቃደኛ መሆኑን ከማሳየት ያለፈ ነገርም አድርጓል። ይህም እግዚአብሔር ፍርዱን በሰዎች ላይ ቢያፈስም እንኳ የእርሱ የሆኑትን ደግሞ እንደሚያድን ያሳያል። የእግዚአብሔር ማዳን የሚገለጠው ጻድቃን ሆነው ለተቆጠሩት ነው። ኖህ ጻድቅ ሆኖ ተቆጥሮ ነበርና ስለዚህም ነጻ ወጣ (**ዘፍጥረት 6:8–9** ይመልከቱ)። እንደዚሁም ሎጥም ጻድቅ ሆኖ ተቆጥሮ ነብርና ስለዚህ እርሱም ነጻ ወጣ (**2 ጴጥሮስ 2:7–9** ይመልከቱ)። እግዚአብሔር እሥራኤላውያንንም ጻድቃን አድርጎ ስለቆጠራቸው ከግብጽ ባርነት ነጻ አውጣቸው። እንደዚሁም ኢየሱስ ጻድቅ ሆኖ ስለተቆጠረ ከሞት ነጻ ወጣ። የውኃ ጥምቀት በጌታ በኢየሱስ ያመነ ሁሉ ከእግዚአብሔር ቁጣ ነፃ መውጣቱን እና ለአዲስ ሕይወት መነሳቱን ያሚያበስር ምሳሌ ነው።





## 18. ሰዎች ለማምለክ እና ለምታዘዝ እንቢ ይላሉ


ከጥፋት ወሃ በኋላ ሰዎች ፍሬያማ እንዲሆኑ፣ እንዲበዙ፣ እንዲባዙና ምድርንም እንዲሞሉ ታዝዘዋል (**ዘፍጥረት 9፡7** ይመልከቱ)። ይህ ደግሞ ለአዳምና ለሔዋን ከተሰጠው ትእዛዝ ጋር ተመሳሳይ ነው (**ዘፍጥረት 1፡28** ይመልከቱ)። እንደ አዳምና ሔዋን ምድርን በእግዚአብሔር ክብር እንዲሞሉ ነበር። ይሁን እንጂ ከጥፋት ውሃ በኋላ የሚኖሩ ሰዎች ይህን አላደረጉም። ይልቁንም እንደ አዳምና ሔዋንም ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በማመጻቸው፤ እግዚአብሔር ሳይሆኑ እግዚአብሔር እንደሆኑ የሚያሳዩ ነግሮች ለማድረግ ወሰኑ። ወደ ሰማይ የሚያደርስንም ግንብ ሠሩ። ይሁን እንጂ እንደምንመለከተው ሁለተኛው ምሳሌ የሚያሳየው የሕዝቡ እቅድ ሳይሳካ መቅረቱን ነው። ምክንያቱም ወደ ሰማይ ግንብ ለመሥራት ያድርጉት ጥረት በጣም አናሳና አቅም ያልነበረው ስለነበር ነው፤ እግዚአብሔርም ደግሞ የሠሩትን ለማየት “መውረድ” ነበረበት (**ዘፍጥረት 11፡7**)። ይህ እራሳቸውን እግዚአብሔር ለማድረግ ለሚሞክሩ ሁሉ ማስጠንቀቂያም ነው። በፍፁም በሰማያት ላይ ገዥ መሆን አይችሉምና። በዘፍጥረት 11 ላይ ባቤል ቢፈርስም፤ የባቤልን ጽንሰ ሀሳብ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ እናገኛለን። ሰዎች ሁል ጊዜ እውነተኛውን አምላክ የማያመልኩበትና የማይታዘዙበት “ቦታ” መገንባት ይፍልጋሉ። የባቢሎን የመጨረሻ ጥፋት በ**ራዕይ 16–17** ላይ ተጠቅሷል። የባቤል ግንብ ታሪክ እውነተኛውን አምላክ ማምለክ ፈቃደኛ ያልሆኑትን ሁሉ እንደ ማስጠንቀቂያ ሆኖ ያገለግላል። እነርሱም እንደ ባቤል ይወድማሉና። እንግዲህ በዚህ መንገድ የባቤል ግንብ ታሪክ ዛሬ ለሰዎች እንደ መልካም ስጦታ ነው። በተጨማሪም ታሪኩ በኢየሱስ ላሉት አማኞች ደግሞ ጠንካራ ማበረታቻ የሚሰጥ ነው። ምንም እንኳን ዓለም እግዚአብሔርን ባለማታዘዝዋ እየተሳካላት እና እግዚአብሔርም የማይመለክበት ቦታ እየገነባች ቢመስልም፤ ይህ ግን አይከናወንም። ምክንያቱም በመጨረሻው የገነባቸው ባቤል ይጠፋልና።



## 19. እግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ሚገነባ የገባው ተስፋ

እባቡ በሴቲቱ ዘር የሚቀጠቀጥ ከሆነ (**ዘፍጥረት 3፡15** ይመልከቱ)፣ ሰዎች እንደገና ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግኙኝነት ይኖራቸውዋል ማለት ነው፣ ስለዚህ እባቡን እንዲቀጠቅጥ የሚመጣው ዘር ከአንድ ሰው የዘር ግንድ መምጣት አለበት። በመሆኑም እግዚአብሔር ይህንን እቅድ ለማሳካት አብራም ከሚባል ሰው ለመጀመር መረጠ (**ዘፍጥረት 11፡27–32** እና **የሐዋሪያት ሥራ 7፡1–8** ይመልከቱ)። አብራም በእግዚአብሔር የተመረጠው ጻድቅ ስለነበር አይደለም፤ ይልቁንስ አብራም እንደማንኛውም በአለም እንደሚኖር ሰው ኃጢያተኛ ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራው እንደራሱ አላማና ፈቃድ ነው (**ኤርሚያስ 13፡11፤ ኢሳይያስ 43፡6–7፤ ኤፌሶን 1፡4–6**)። እግዚአብሔር ለአብራም ዘሩ እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ እንደሚበዛ ቃል ገባለት። በተጨማሪም ይህ ሰው እና ዘሩ ምድርን እንደሚወርሱ ቃል ገብቶለታል (**ሮሜ 4፡13** ይመልከቱ)። እነዚህ ተስፋዎች በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በሙሉ ተጠቅሰው እንናገኛለን። በመጀመሪያ የተነገሩት እና የተገለጹት በ**ዘፍጥረት 12፡1–3፣ 13፡14–17፣ 15፡1–5፤ 18–21፣ 17፡1–14፣ 18፡16–19፣ 22፡15–18 እና 24፡7** ላይ ነው። የአብራም ስም ከጊዜ በኋላ ወደ አብርሃም ተቀየረ። አብርሃም የተስፋውን ክፍል መፈጸም ሲጀምር ማየት ቢችልም እንኳ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ተስፋ ግን በአብርሃም ዘመን ሙሉ በሙሉ አልተፈጸመም ነበር። አብርሃም ግን ተስፋው እንደሚፈጸም ያውቅ ነበር፣ ነገር ግን በእርሱ ዘመን ፍጻሜያቸውን ለማየት አልታደለም ነበር (**ዕብራውያን 11፡8–12** ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ከብዙ ዘመናት በኋላ በኢየሱስ ዘመን ተፈጽመዋል፣ ምክንያምቱም ኢየሱስ የአብርሃም ወራሽ ነውና (**ማቴዎስ 1፡1 እና የሐዋሪያት ሥራ 13፡32–33** ይመልከቱ)። ደግሞም ክርስቲያኖች "በክርስቶስ" ስለሆኑ እኛ ደግሞ እንደ አብርሃም ዘር ተቆጠርን (**ገላትያ 3፡7–29** ይመልከቱ)።

አብርሃም እውነተኛ ሰው ነበር። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ 2100 አካባቢ የኖረ ሰው ነው። አብርሃም እንደሌሎችም ሰዎች ኃጢአተኛ ሰው ነበር። በእግዚአብሔርም የተመረጠው በጽድቁ ወይም በመልካም ሥራው አልነበረም። ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱን የመረጠው እንዲያው እግዚአብሔር ሊመርጠው ስለፈለገ ብቻ ነው። አብርሃም ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ነበርው። በእምነቱም ምክንያት ጻድቅ ሆኖ ተቆጠረ (**ዘፍጥረት 15፡6 እና 18፡14** ይመልከቱ)። ኢየሱስ ደግሞ የአብርሃም ልጅ መሆኑን ታውጇል። ይህ ማለት ደግሞ ለአብርሃም የተገባለት ተስፋ ወራሽ ነው ማለት ነው ( እንደገና **ማቴዎስ 1፡1** ይመልከቱ)።



## 20. የአብርሃም የመጀመሪያ ዘሮች

እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ተስፋ ለልጁ ለይስሐቅ ተድግሟል (እስማኤልም በዚህ ምሳሌ ውስጥ ተገልጿል) እና በኋላም ለይስሐቅ ልጅ ለያዕቆብ (**ዘፍጥረት 26፡4፣ 24፣ 28፡13–14** ይመልከቱ)። ያዕቆብ 12 ልጆች ነበሩት። ከእነዚህም 12 ልጆች የእግዚአብሔር ሕዝብ "ተገነባ"። በዚህም መሠረት ዘፍጥረት የእግዚአብሔር ሕዝብ በቁጥር መብዛት የጀመረበትን ታሪክ ያወሳል። ምክንያቱም እግዚአብሔር አንድ ቀን እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደሚበዙ ቃል ስለገባላቸውም ጭምር ነው። የዘፀአት ጸሐፊ (ሙሴም) በእስራኤል ሕዝብ መብዛት ደጋግሞ በመጥቀስ በጣም መመሰጡን እንመለከታለን (**ዘፀአት 1፡7፣ 12፣ 20** ይመልከቱ)። ይህም የሆነበት ምክንያት ሙሴ ስለእነዚህ ተስፋዎች ስለሚያውቅና እግዚአብሔርም ወደ ፍጻሜያቸው እንደሚያመጣቸው ስለሚያምንም ነው። እንደዚሁም ደግሞ የሐዋሪያት ሥራም ጸሐፊ በቤተ ክርስቲያን መስፋት በጣም ተመስጦ እንደነበር ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመሆን እሥራኤልን ስለተካች አይደለም። ነገር ግን እውነተኛው እሥራኤል ክርስቶስ ስለሆነ እና በእርሱም ውስጥ የተቆጠሩት ሁሉ እንደዚሁ ስለሆኑ ነው እንጂ። በዚህ መንገድ የብሉይ ኪዳን ዘመን ቅዱሳንና የአዲስ ኪዳን ዘመን ቅዱሳን ተገናኝቷል! እንግዲህ ለመቁጠር የሚያዳግተውን ሰዎች በተመለከተ እግዚአብሔር የገባው ተስፋዎችም ይፈጸማሉ ማለት ነው (**ራዕይ 7፡9** ይመልከቱ)።



## 21. እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ያየው ነቢይ

ሙሴ የተነሳው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነፃ አውጪ ሆኖ ነበር። ከግብፅ አውጥቶ ወደ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላቸው መልካም ሥፍራ እንዲወስዳቸው ተጠርቶ ነበር። በዚህ መንገድ ሙሴ የክርስቶስ **ምሳሌ** ነበር። ይህም ማለት እርሱ በብዙ መንገድ እንደ ክርስቶስ ነበር ማለት ነው። ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሰይጣንና ከኃጢአት ባርነት ነፃ አውጥቶ ወደ እግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ይመራቸዋል (**ኤፌሶን 2፡1–10** ይመልከቱ)። ልክ እንደ ሙሴ፣ ክርስቶስም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት የተነሳው ከወንዝ ነበር። በተለይም ሙሴ ነቢይ በነበረበት ውቅት ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት መነጋገር በመቻሉ ምክንያት ከሌሎች ነቢያት የተለየ ነበር (**ዘፀአት 33፡11** ይመልከቱ)። በ**ዘዳግም 18፡15–18**፣ ሙሴ "እንደ እርሱ" የሚሆን ሌላ ነቢይ እግዚአብሔር እንደሚያስነሳ ተንብዮ ነበር። ይህም ማለት ይህ የሚነሳው ነቢይ እንደ ሙሴም እግዚአብሔርን ፊት ለፊት የሚያይ ነው ማለት ነው። ደግሞም ሙሴ ሕዝቡ የሚመጣውን ይህን ነቢይ መስማት እንዳለባቸው አስጠንቅቆ ነበር። ምንም እንኳን በብሉይ ኪዳን ብዙ ነቢያት የተነሱ ቢሆንም እንኳ አንዳቸውም ግን በዚህ መንገድ እንደ ሙሴ አልነበሩም (**ዘዳግም 34፡10–12** ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ግን በዚህ መንገድ እንደ ሙሴ ነው። እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ያያል። ስለዚህ እርሱን ልንሰማው ይገባል (**ማርቆስ 9፡7** ይመልከቱ)።

ሙሴ እውነተኛ ሰው ነበር። በ 1, 406 ዓክልበ አካባቢ እንደሞተ ይገመታል። ስለዚህ የሙሴ መጽሐፍ (ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም) የተጻፈው ምናልባትም በ 1, 446–1, 406 ዓክልበ አካባቢ ሊሆን ይችላል። ከንግግሩ እንደ ምንረዳው ዘዳግም 33 እና 34ን የጻፈው ስሙ ያልተጠቀሰው አርታኢ ከሙሴ በኋላ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዓመታት እንደ ኖረ ግልጽ ነው። አርታኢውም ደግሞ የክርስቶስን መምጣት የሚጠብቅ የእምነት ሰው ነበር።




## 22. የእግዚአብሔር ሕዝብ በግብፅ

በሴቲቱ ዘር (በእግዚአብሔር ሕዝብ) እና ( ሰይጣንን በሚከተሉ ሰዎች) መካከል የተደረገው ጦርነት እሥራኤላውያን በግብፅ በባርነት በነበሩበት ወቅት በሚያስገርም መልኩ ታይቷል። የእግዚአብሔር ሕዝብ በግብፅ ለ400 ዓመታት በባርነት ኖሯል (**ዘፍጥረት 15፡13–14** እና **የሐዋሪያት ሥራ 7፡9–53** ይመልከቱ)። ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ልጅ በምድር ላይ የእግዚአብሔር ተወካዮች እንዲሆኑ እና የእግዚአብሔርንም መልካምነት በምድር ላይ እንዲበዛ ቢያደርጉም፤ ይህ ማለት ደግሞ ምንም ችግር አይደርስባቸውም ማለት ደግሞ አይደለም። እሥራኤልውያን በግብፃውያን እጅ እጅግ ተሠቃይተዋል (**ዘፀአት 1፡18–22** ይመልከቱ)። ፈርዖን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት ሞክሮ ነበር (**ዘፀአት 1** ን ይመልከቱ)፤ ነገር ግን እግዚአብሔር "ልጁን" (እሥራኤልን) ከግብፅ አወጣው። እሥራኤል የክርስቶስ "ምሳሌ" ናት። እንደ እሥራኤልም ደግሞ እግዚአብሔር ክርስቶስን ከግብፅ አወጣው (**ማቴዎስ 2፡13–15** ይመልከቱ)። "በእርሱ ያሉቱ" ሁሉ፣ "በክርስቶስ" ስለሆኑ፣ ከሰይጣን እና ከኃጢአት ባርነት አምልጠዋል (**ኤፌሶን 2፡1–10** ይመልከቱ)።



## 23. በግብፅና በአማልክቶቿ ላይ የተደረጉ አሥር ፍርዶች

የእሥራኤል ሕዝብ የዳኑት በመልካም ሥራቸው ወይም በወታደራዊ ጥንካሬያቸው አይደለም። ነገር ግን የዳኑት በእግዚአብሔር ጸጋ አማካኝነት ነው። የእግዚአብሔር ፍርድ በግብፅ ላይ በተከታታይ መቅሰፍቶችን አፈሰሰ (**ዘፀአት 4–12** ይመልከቱ)። በግብፅ ላይ የወረደው መቅሰፍት በአገላለጽ ከፍጥረት ታሪክ ተቃራኒ ነው (**ዘፍጥረት 1** ይመልከቱ)። ፍጥረትን **እንደማጥፋት** ዓይነት ነበሩ ማለት ይቻላል። እንደዚሁም ደግሞ መቅሰፍቶቹ የእግዚአብሔርን ኃይል እና የእግዚአብሔር ቁጣ በኃጢአትና በጣዖት አምልኮ ላይ እንደተገለጠ ትንሽ ማሳያም ነበሩ። መቅሰፍቶቹም ደግሞ በግብፅ አማልክት ላይ እግዚአብሔር የበላይ እንደሆነ አሳይተዋል (**ዘፀአት 12፡12** ይመልከቱ)። እያንዳንዱ መቅሰፍት በሆነ መንገድ በግብፅ በተከበረው የአማልክት ኃይል ላይ ያፌዘ ነበር። ለምሳሌ በግብፅ ውስጥ ፀሐይን ያመልኩ ነበር። ስለዚህ የግብፅ አማልክት በእውነተኛው አምላክ ላይ ምንም ሥልጣን እንደሌላቸው ለማሳየት አንዱ መቅሰፍት ጨለማ ነበር። መቅሰፍቶቹ ለግብፃውያን ወደ እግዚአብሔር መመለሻ ጸጋው ነበሩ። ይህ ማለት የመጨረሻ ፍርድ በእነርሱ ላይ ከመምጣቱ በፊት ንስሐ መግባት እንደሚያስፈልጋቸው ማስጠንቀቂያ ነበር ማለት ነው። እንደዚሁም መቅሰፍቶቹ ለእሥራኤላውያንም ጸጋው ነበሩ። ምክንያቱም መቅሰፍቶቹ በሚፍሱበት ጊዜ እግዚአብሔር በመቅሰፍቱ እንዳይጎዱ እሥራኤልን ጠብቆዋልና። መቅሰፍቶቹ በዚያን ጊዜ ለተቀረው ዓለምም ቢሆን ጸጋው ነበሩ። ማለት የተቀረው ዓለምም ንስሐ እንዲገባ አለበለዚያ እንደ ግብፅም እንደሚቀጡ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የጸጋው ማስጠንቀቂያ ነበሩ። አሁን ላለውም ዓለም ቢሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የጸጋው ማስጠንቀቂያ ናቸው። ምድር ስለጣዖት አምልኮቷ ንስሐ መግባት አለባት አለበለዚያ እንደ ግብፅ ትጠፋለችና። በግብፅ ላይ የፈሰሱት መቅሰፍቶች በኃጢአቷና በጣዖት አምልኮቷ ምክንያት በዚህ ዓለም ሁሉ ላይ ሊፈሱ ያሉትን መቅሰፍቶች የሚያሳይ ትንሽ ሥዕል ነበር። ይህ ሊመጣ ስላለው አለማቀፋዊው መቅሰፍቶች በ**ራዕይ 6፤ 8–9፤ 15–18** ውስጥ መመልከት ይቻላል።



## 24. በቀይ ባሕር ውስጥ መዳንና መጥፋት

የእሥራኤል ሕዝብ ከግብፅ ባመለጡ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ሆን ብሎ በቀይ ባሕር በኩል እንዲያልፉ መንገዳቸውን አቀናው። ቀይ ባሕርን እንዴት እንደተሻገሩ በ**ዘፀአት 14** ላይ ተጠቅሷል። በ**ዘፀአት 15፡1–21** ደግሞ በድጋሚ በግጥም መልክ ተጽፏል። ይህ ግጥም ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚነገርው ታሪክ በጣም ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም ግጥሙ በ**መዝሙር 118፡14፣ በኢሳይያስ 12** እና በ**ራዕይ 15፡2–4** ላይ ተደጋግሞ ተጽፏል። ከዚህ ግጥም የመጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች ክፍሎች የጠቀሱት ደግሞ የመጀመሪያው የቀይ ባሕር መሻገር እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለሕዝቡ ሁሉ የሚሰጠውን የደኅንነት እና የወንጌል ክስተት **ምሳሌ** እንደሆነ በሚያሳይ መልኩ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ በቀይ ባሕር ሲድኑ፤ የእግዚአብሔር ጠላቶች ደግሞ በቀይ ባሕር ወድመዋል (**ዘፀአት 14፡23–31** ይመልከቱ)። ስለዚህ፤ ልክ በዘፍጥረት 6–8 ላይ እንዳለው የጥፋት ውሃ፣ ቀይ ባሕር የድነትና የፍርድ ምልክት ነው። የቀይ ባሕር ታሪክ ለዓለም ፀጋው ነው። አለም ይህንን ታሪክ ሰምቶ ንስሐ መግባት አለበት። ይህ በኢያሱ ዘመን በረዓብ ላይ ሆኗል (**ኢያሱ 2፡10** ይመልከቱ)። በውሃ መጠመቅ አንድ ክርስቲያን በክርስቶስ ምክንያት ያገኘው ነፃ የመውጣት ምሳሌ ነው። ልክ የእግዚአብሔር ሕዝብ በቀይ ባሕር ውሃ ውስጥ እንዳለፈ፤ ክርስቲያንም በጥምቀት ውሃ ውስጥ ያልፋል ማለት ነው።



## 25. የእግዚአብሔር ሕዝብ በምድረ በዳ

በቀይ ባሕር ካለፉ በኋላ ሕዝቡ በቀጥታ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል ወደገባላቸው ምድር አልገቡም። ይልቁንም በምድረ በዳ “ተፈተኑ”። ይህ የምድረ በዳ ጉዞ ከ**ዘፀአት** 16 ጀምሮ ተገልጿል፡ እንዳውም የምድረ በዳው ጊዜ እስከ ዘዳግም መጨረሻ ድርስ አላበቃም ነበር። ምንም እንኳን ሕዝቡ እግዚአብሔር በተናገረላቸው የተስፋይቱ ምድር ውስጥ ባይኖሩም፤ በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ለእነርሱ በዝቶ ነበር። በዙ ጊዜ እግዚአብሔር በምሕረትና በይቅርታ ታግሶዋቿል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚበሉትን ምግብ ከሰማይ ሰጣቸው። ይህም ምግብ መና ተብሎ ይጠራ ነበር (**ዘፀአት** 16 ይመልከቱ)። ደግሞ ውሃ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከዐለት ድንጋይ ውኃ አወጣላቸው (**ዘፀአት** 17 ይመልከቱ)። እንደዚሁም እግዚአብሔር ተገለጠላቸውና በሕይወትም ይኖሩ ዘንድ መልካሙን ሕጎች ሰጣቸው (**ዘፀአት** 20 ይመልከቱ)። በተጨማሪም እግዚአብሔር ለሙሴ የማደሪያውን ድንኳን እንዴት እንደ ሚሰራ ራዕይ ሰጠው፤ የማደሪያው ድንኳኑንም ለሚያንጹ ሰዎች ልዩ ስጦታ ሰጣቸው (**ዘፀአት** 26 ይመልከቱ)። እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገው ቸርነት ቢኖርም በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ግን ሕዝቡ በእግዚአብሔር አልታመኑም። እንዳውም ይባስ ብለው ብዙ ጊዜ አጉረመረሙ፣ አልታዘዙምም። ይህ ባሕሪያቸው እግዚአብሔርን አላስደነቀውም፤ ምክንያቱም እንደማይታዘዙ ያውቅ ነበርና። እንዲያውም ሙሴ የእግዚአብሔር ሕዝብ ባለመታዘዛቸው ከተስፋይቱ ምድር የሚባረሩበት ጊዜ እንደሚመጣ ተናግሮ ነበር (**ዘዳግም** 31፡16–17 ይመልከቱ)። ባለመታዘዛቸው ምክንያት ከግብፅ የወጣው የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ (ከኢያሱና ከካሌብ በቀር) እስኪሞቱ ድርስ የምድረ በዳው ጊዜ ለ40 ዓመታት ረዘመ። በእግዚአብሔር ባለመታመናቸው፣ ሕዝቡ እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላቸው መልካም ቦታ እንዲገቡ አልተፈቀደላቸውም ነበር (**ዕብራውያን** 3 እና 4 ይመልከቱ)።

እግዚአብሔር ለእሥራኤል በምድረ በዳ ያድረገላቸው ተአምራዊ እንክብካቤ ክርስቲያኖች በክርስቶስ የተደረገላቸው እንክብካቤ **ምሳሌ** ነው። ለምሳሌ ክርስቶስ ከሰማይ የወረደ እንጀራ ነው (**ዮሐንስ** 6፡22–59 ይመልከቱ)። እንደዚሁም ደግሞ ልክ ከዐለት ድንጋይ ውሃ እንደጠጡ፤ እውነተኛ መንፈሳዊ “ውሃ” የሚመጣው ደግሞ ከክርስቶስ ነው (1 **ቆሮንቶስ** 10፡4 ይመልከቱ)።



## 26. የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ብቻ ለማምለክ ፈቃደኞች አልነበሩም

ምንም እንኳን እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ነፃ አውጥቶ እርሱነቱን በቸርነቱ ቢገልጥላቸውም፤ ሕዝቡ ግን ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበሩም። ማንኛውንም ምድራዊ ነገር የእግዚአብሔርን መልክ መስለው መፍጥር አልነበርባቸውም። እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ በመሆኑ ምንም ምድራዊ ነገር እርሱን ሊወክል አይችልምና። እግዚአብሔር የሚመለከው እርሱ እንዲመለክ በፈለገው መንገድ ብቻ ነው። ይህም እምነትን ይጠይቃል። ሕዝቡ ግን እግዚአብሔርን እነርሱ በፍለጉት መንገድ ማምልክ ፈለጉ። ምድራዊ ፍጡር እስኪመስል ድረስ የእግዚአብሔርን ክብር “አዋረዱ”። ሕዝቡ እግዚአብሔርን ከመታዘዝና በመንገዱም ከመሄድ ይልቅ እነርሱ በፈለጉት መልክ እግዚአብሔርን አስመስለው ለመፍጠር ሞከሩ (**ዘፀአት 32** ይመልከቱ)። በወርቅ ጥጃው ምክንያት ብዙ ሰዎች ከተገደሉ በኋላም ቢሆን ሕዝቡ ግን አሁንም ጣዖትን የመከተል ፍቅር ነበራቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ክብሩን ከሌላ አማልክት ጋር አይካፈልም (**ዘዳግም 4፡23–24** ይመልከቱ)። እርሱ “የሚባላ እሳት ቀናተኛ አምላክ” ነውና። ዛሬም ቢሆን እንዲሁ ነው።

እሥራኤላውያን በኋላ ወደ ተስፋዪቱ ምድር ወደ እስራኤል በተሻገሩበት ጊዜ እንኳን የጣዖት አምልኮት ያደርጉ ነበር (ለምሳሌ **1 ነገሥት 12፡28–30** ይመልከቱ)። ሕዝቡ ጣዖቶቻቸውን ፈጽመው አልተውም ነበር። በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳላቸው ቢናግሩም፤ ይሁን እንጂ እንደ በኣል በመሳሰሉት ሌሎች አማልክቶች ይታመኑ ነበር (**1 ነገሥት 18፡21** ይመልከቱ)። ሐሰተኛ ነቢያት ደግሞ ይህን ዓይነቱን አምልኮት ያበረታቱ ነበር። በተቃራኒው ደግሞ የእግዚአብሔር እውነተኞቹ ነቢያት እሥራኤል በጣዖት አምልኮት ምክንያት በደለኛ እንደነበሩና ንስሐ መግባት እንዳለባቸው አለዚያ እንደ አዳምና ሔዋንም ከምድራቸው እንደሚባረሩ ያውጁ ነበር (**ሆሴዕ 2፡2–13** ይመልከቱ)። ጣዖትን በመወደድ ፍቅራቸው እንዳይቀጥሉ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር አዲስ ቃል ኪዳን ተደረገ። ነቢያት ደግሞ ይህ አዲስ ኪዳን እውን የሚሆንበትን ቀን ደጋግመው ይናገሩ ነበር (**ሆሴዕ 2፡16–20** ይመልከቱ)። ይህም የተባለው አዲስ ኪዳን የጀመረው በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው (**ሉቃስ 22፡20**)።



## 27. ዐሥርቱ ትዕዛዛት

በሙሴ ዘመን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ጠንካራ ስምምነት አድርጓል። ይህም ብሉይ ኪዳን በመባል ይታወቃል። ብሉይ ኪዳን የተባለበት ምክንያት እግዚአብሔር ወደፊት ከሕዝቡ ጋር አዲስ ቃል ኪዳን "እደሚፈጽም" ቃል ገብቶ ስለነበረ ነው። አዲስ ቃል ኪዳን አስፍለጊ የሆነው በአሮጌው ኪዳን ችግር ምክንያት አይደለም። ይልቁንም አዲስ ቃል ኪዳን አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት አሮጌው ቃል ኪዳን የሰዎችን ልብ ሊለውጥ ባልምቻሉ ነው እንጂ። ደግሞም ችግሩ የሕዝቡ ነበር እንጂ የኪዳኑ አልነበረም። ሕዝቡ ብሉይ ኪዳንን በመጠበቅ ታማኝ ቢሆኑ ኖሮ፤ የእግዚአብሔርን መገኘት ለተቀረው ዓለም የሚያምጣ "የመንግሥት ካሕናት" እና "የተቀደሰ ሕዝብ" ይሆኑ ነበርና (**ዘፀአት 19፡5–6** እና **ዘዳግም 4፡ 5–8** ይመልከቱ)። እሥራኤል በኃጢአተኛ ሰዎች እና በእግዚአብሔር መካከል አስታራቂ ሆና ማገልገል ነበረባት። ይህ ግን አልሆነም።

የብሉይ ኪዳን መሠረት "ዐሥርቱ ትእዛዛት" ናቸው (**ዘፀአት 20፡1–17** ይመልከቱ)። እነዚህም በሁለት ጎራ ሊከፈሉ ይችላሉ። ከዐሥርቱ ትእዛዛት አንዳንዶቹ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ግኑኝነት ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመልከቱ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ሰዎች ከጎረቤቶቻቸው ጋር ስለሚኖራቸው ግኑኝነት የሚናገሩ ናቸው። ከዐሥርቱ ትእዛዛት በኋላ ያሉትን የተቀሩት ሕጎች ደግሞ ዐሥርቱ ትእዛዛት እንዴት በማሕበራዊና በኃይማኖታዊ መንገዶች መተግበር እንደሚገባ የሚገልጹ ናቸው።


የዐሥርቱ ትእዛዛት መሰጠት በተመለከት በሙሴ መጽሐፍ (ዘፍጥረት–ዘዳግም)፡ በ**ዘፀአት 20** እና በ**ዘዳግም 5** ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። እነዚህ ሁለቱም ክፍሎች መጠናት ይኖርባቿዋል።

በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች በብሉይ ኪዳን ሥር እንዳልሆንን መገንዘብ አስፈላጊ ነገር ነው። ምክንያቱም የክርስቶስ መምጣት የብሉይ ኪዳንን ፍጻሜ አመጣ፤ እንደዚሁም ደግሞ አዲስና የተሻለ ቃል ኪዳን አስጀመረ (**ኤርሚያስ 31፡31–34፤ ሕዝቃኤል 36፡24–27፤ ዕብራውያን 8፡13** እና **10፡9** ይመልከቱ)። ስለዚህ ክርስቲያኖች የሚኖሩት በዚህ አዲስ ቃል ኪዳን ሕግ ሥር ነው ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ክርስቲያኖች በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደ ነበሩት የእግዚአብሔር ሰዎች ከዐሥርቱ ትእዛዛት ሥር አይደሉም። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን መልካሙን ትእዛዛት መታዘዝ የሚችሉት የክርስቶስን መንፈስ በውስጣቸው ስለሚኖር ነው።



## 28. በቸርነቱ የተሰጠ የካህናት ጸጋ


እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ ነው። ይህ እንዲሆን ደግሞ ሰዎች ቅዱሳን መሆን አለባቸው ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና (**ዘሌዋውያን 11፡44 እና 1 ጴጥሮስ 1፡15–16** ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ በኃጢአት ምክንያት ሰዎች ከእግዚአብሔር ህልውና መገኘት ርቀው ለመኖር ተገደዱ። በሙሴ ዘመንና ከዚያም በኋላ ለሚኖሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት መንገድ የሚገልጽ ቃል ኪዳን ተዘጋጅቶ ነበር። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦቹ ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ይፈለግ ነበር። ይሁን እንጂ በአዳም ኃጢአት ምክንያት፤ ወደ እግዚአብሔር መገኘት መድርስ ለሁሉም ሰው "ወዲያውኑ" ክፍት አልነበርም። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት የሰዎች ኃጢአት "መሸፈን" ነበረበት። እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና ወደ እርሱ መቅረብ የሚችሉት ኃጢአታቸው በትክክል "የተሰረየላቸው" ሰዎች ብቻ ናቸው። ኃጢአታቸው እንዲሰረይላቸው ደግሞ **ንስሐን፣ መባን፣ መስዋዕትን** እና እነዚህን መስዋእቶች ደግሞ ለእግዚአብሔር የሚያቀርብ **አስታራቂ** ያስፈልግ ነበር። ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል አስታራቂ ሆነው እንዲያገለግሉ ካህናት የተባሉ ሰዎች ተነሱ። እነዚህም የብሉይ ኪዳን ካህናት ከሌዊ ነገድ የመጡ ነበሩ። ከእነርሱም ውስጥ "ሊቀ ካህን" የሚባል አንድ ልዩ ካህን ነበረ። እርሱ ብቻውን ወደ ማድሪያው ድንኳን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት ይችል ነበርና። ይህን ደግሞ ማድረግ የሚችለው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። ሊቀ ካህናቱ የክርስቶስ "ምሳሌ" ነበር። ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ የሚማለድ እውነተኛ ሊቀ ካህናት ነው (**መዝሙር 110** እና **ዕብራውያን 5፡1–10** ይመልከቱ)። በዚህ ዘመን ያሉ ክርስቲያኖችም ካህናት ናቸው (**1 ጴጥሮስ 2፡5** እና **ራዕይ 1፡6** ይመልከቱ)። ክርስቲያኖች ካህናት የሆኑት ደግሞ ከሌዊ ነገድ ስለሆኑ አይደለም። ነገር ግን ካህናት የሆኑት "በክርስቶስ" ስላሉ ነው። በዚህም ምክንያት በአዲስና በተሻለ የክህነት አገልግሎት ያገለግላሉ ማለት ነው።



## 29. የእግዚአብሔር ማደሪያ በምድር ላይ

እግዚአብሔር በእርሱና በሕዝቡ መካከል ኅብረት እንዲኖር እና ሰዎች ክብሩን በምድር ሁሉ እንዲያመጡ ይፈልግ ነበር። ነገር ግን ይህ በአዳም ኃጢአት ምክንያት በኤደን ገነት አልተሳካም። በዚህም ምክንያት ደግሞ አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ መቆየት አልቻሉም። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሥልጣን ላላመቀበል ቢፈልጉም እንኳ እግዚአብሔር ግን በቸርነቱ ሰዎች ከእርሱ ጋር የሚገናኙበትን መንገድ ደግሞ አዘጋጅቷል። የማደሪያው ድንኳን እግዚአብሔር እና ሰዎች የሚገናኙበት ቦታ መሆን ነበረበት። በዘፀአት ውስጥ ስላለው ስለማደሪያው ድንኳን የሚናገሩ 13 ምዕራፎች አሉ (**ዘፀአት 25–31** እና **35–40** ይመልከቱ)። ይህም የሚያሳየው እግዚአብሔርና ሰዎች በንድነት የሚኖሩበት ሥፍራ ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ ነው። የማደሪያ ድንኳን በውስጡ የብዙ ፍራፍሬዎች ምስል ነበሩት። ይህም  የማደሪያው ድንኳን የኤደን ገነት ነጸብራቅ እንደነበረ የሚያሳይ ነው። የማደሪያው ድንኳን ተንቀሳቃሽ ነበር [ማለትም ጉዞ ሲጀምሩ አፍርሰው ይይዙታል ከጉዞ ሲያርፉ ደግሞ መልሰው የሚተክሉት ነበር]። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር የሚንቀሳቀስ ነበር። በኋላ ግን ቤተመቅደስ ተብሎ በሚጠራው ቋሚ መዋቅር ተተካ። እንደገና በኋላ ይህ ሕንፃ በኢየሱስና በቤተክርስቲያን ተተካ (**ዮሐንስ 2፡18–22፣ ኤፌሶን 2፡19–22 እና 1 ጴጥሮስ 2፡4–5** ይመልከቱ)። በኤደን ገነት ውስጥ ፍራፍሬ እንደነበር ሁሉና እንደዚሁም የማደሪያ ድንኳን ውስጡ በፍሬ የተንዥጎረጎረ እንደነበር፤ ቤተክርስቲያንም ለተቀረው ዓለም የሚታይ ፍሬ አላት (**ገላትያ 5፡22–23** ይመልከቱ)።

የማደሪያው ድንኳን ግንባታ በተመለከተ ሰባት ገለጻዎች አሉ። እነዚህ ሰባት ገለጻዎች ፍጥረት ከተፈጥረባቸው ሰባት ቀናት ጋር ይዛመዳሉ (**ዘፀአት 25፡1፣ 30፡11፣ 17፣ 22፣ 34፣ 31፡1፣ 12** ይመልከቱ)። ፍጥረት በተጀመረ በስድስተኛው ቀን እግዚአብሔር ሁለት ሰዎችን ፈጠረና የእግዚአብሔርን መልክ በምድር ላይ እንዲያንጸባርቁ ተልዕኮ ሰጣቸው። ስለዚህ የአትክልቱ ሥፍራ የነበርውን የእግዚአብሔር መገኘት ወደ ምድር ሁሉ ማምጣት ነበረባቸው። ከመገናኛው ድንኳን ጋር በተገናኘው ስድስተኛው ገለጻ ላይ ደግሞ (**ዘፀአት 31፡1**)፣ ለማደሪያ ድንኳን ግንባታ ሁለት ሰዎች እንደ ተለዩ ያስረዳል። በፍጥረት በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ዐረፈ። እንደዚሁም በሰባተኛው ገለጻ (**ዘፀአት 31፡12–17**) ላይ ደግሞ እግዚአብሔር እሥራኤላዎያንን ሰንበትን እንዲጠብቁ አዟል። ሙሴ ምን እንደሚጽፍ እንደሚያውቅ ግልጽ ከመሆኑም በላይ ሙሴ የሚያደርጋቸውን ተያያዥ ነገሮች አንባቢዎቹ እንዲረዱ ይፈልግ እንደ ነበረም ግልጽ ነው። ሙሴ ይጽፈው የነበረውን በማወቁ ክርስቲያኖች ሊደነቁ አይገባም። ሐዋሪያው ጴጥሮስም ነቢያት ሁሉ ይጽፉት የነበርውን ያውቁ እንደነበር በግልጽ ተናግሯል (**1 ጴጥሮስ 1፡10–12** ይመልከቱ)።



## 30. የእሥራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ማመን አልፈለገም

በሥዕሉ ላይ እንደ ተመለከተው እሥራኤላውያን የዮርዳኖስ ወንዝ ከመሻገራቸው በፊት ወደ ተስፋይቱ ምድር የሄዱት የ12ቱ ሰላዮች ምሳሌ ነው። 12ቱ ሰላዮች ደግሞ 12ቱን የእሥራኤል ነገዶች ይወክላሉ። እነዚህ ሰላዮች የተላኩት እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደሚሰጥ ቃል ወደገባለት ምድር ነበር፤ ስለዚህ ሕዝቡ ገብተው ይወርሱት ዘንድ ስለ ምድሩ ወሬ እንዲያመጡ ታስቦ ነበር። ይሁን እንጂ በሥዕሉ ላይ እንደ ምንመለከተው ግን ሰላዮቹ በተለያየ ቀለም እንደ ተለዩ ሁሉ ሁሉንም እግዚአብሔርን የሚከተሉ አልነበሩም። 10ሩ ሰላዮች ሲጠብቃቸው ለነበረው ለእሥራኤል ሕዝብ መጥፎ ወሬ አመጡ። ጥሩ ዜና ያመጡት ከሰላዮቹ ሁለቱ ብቻ ነበሩ። ሕዝቡ ደግሞ መጥፎ ዜና ይዘው የመጡትን በመስማት እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ ቀሩ። በዚህም ምክንያት ከዚያ ትውልድ ጀምሮ ሁሉንም እስኪሞት ድረስ ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ ተቅበዘበዙ (**ዘኍልቁ 13–14** ይመልከቱ)። የእግዚአብሔርን መልካም ተስፋዎች ያመኑ ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ – ኢያሱና ካሌብ። የካሌብን እምነት በተመለከተ **ኢያሱ 14፥6–12** ይመልከቱ።




## 31. ለአርባ አመታት መጠበቅ፣ መንከራተት፣ መከተልና መሞት

በኃጢአት ምክንያት፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር ወዲያውኑ እንዲገቡ አልተፈቀደላቸውም። በእግዚአብሔር መልካሚቱ ቃል ለመታመን ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት የእሥራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ ለ40 ዓምታት ለመቅበዝበዝ ከመገደዳቸውም በላይ ጎልማሳ የነበርው ትውልድ ደግሞ በሙሉ ሞቶ አለቀ። የ 40 ዓምቱ የመንከራተት ጊዜ በአሪት ዘኁልቁ መጽሐፍ ውስጥ ተገልጿል። በዚህም ጊዜ እንኳን ቢሆን እንግዚአብሔር ለሕዝቡ ታልቅ ምሕረትን አሳይቷል።



## 32. ለሕዝቡ ሦስት ረጃጅም ስብከት በሙሴ ዘመን . . . እና ዛሬ

የዘዳግም መጽሐፍ ሦስት ረጃጅም ስብከቶችን ያካተተ ነው። ከ40 ዓመታት ቆይታ በኋላ በምድረበዳ  እና የእሥራኤል ሕዝብ ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ተስፍዪቱ ምድር ከመግባታቸው በፊት በሙሴ የተሰበኩ ነበሩ። በእግዚአብሔር መልካም ሥፍራ የነበርው ሙሴ የሕይወት "ሕጎች" ተናግሯል። ምንም እንኳን ሙሴ ሕዝቡ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ቢናገርም ሕዝቡ ግን የእግዚአብሔርን ሕግጋት መጠበቅ እንደማይችሉ ያውቅ ነበር። ስለዚህ እንደሚያምፁና ደግሞም እንደ አዳምና ሔዋንም ከእግዚአብሔር መልካም ቦታ እንደሚባረሩ ያውቅ ነበር (**ዘዳግም 31፡27–29** ይመልከቱ)። እንደዚሁም ሙሴ እግዚአብሔር ንስሐ ከገቡ በኋላ  ሕዝቡን በጸጋው ወደ ራሱ እንደሚመልስ ያውቅ ነበር። በተጨማሪም እግዚአብሔር እንደ ሙሴ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት የሚያይ አዲስ ነቢይ የሚያስነሳበት ዘመን ይህ ጊዜ እንደሚሆን ሙሴ ይገነዘብ ነበር (**ዘዳግም 18፡15–19** ይመልከቱ)። ይህም "ነቢይ" ኢየሱስ ነው (**ዮሐንስ 1፡21፣ 6፡14፣ 7፡40፣ የሐዋሪያት ሥራ 3፡22–23** ይመልከቱ)። የዘዳግም የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች የተጻፉት ሙሴ ከሞተ በኋላ የራሱን አስተያየት "በጨመረ" ሌላ አርታኢ አማካኝነት ነው። ይህ ሰው በእግዚብሔር የሚታመን ነበር እናም ደግሞ በሙሴ ጽሑፎች ውስጥ የተነገረለትን የክርስቶስ መምጣት ደግሞ ይጠባበቅም ነበር።



## 33. ሕጉ ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር እንዴት እንድሚዛመድ

ሕጉ (ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም) ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሁሉ የተለይ ነው። ሆኖም በኋለኞቹ ላይ ያሉት ጸሐፊዎች በእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ሕጉን በመደጋገም ሲጠቅሱ ይስተዋላል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉትን ሁለቱንም ክፍሎች ሕጉን ይጠቅሳሉ፣ እንደዚሁም ደግሞ ሰዎች በሕጉ የተጻፍትን እንዲታዘዙም ጥሪ ያቀርባሉ። ይህ በአዲስ ኪዳንም እውነት ነው።